
# Colours/ቀለማት



| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| brown<br>ቡኒ | green<br>አረንጓዴ | grey<br>ግራጫ | yellow<br>ቢጫ | blue<br>ሰማያዊ | red<br>ቀይ |



| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| orange<br>ብርቱካናማ | purple<br>ወይንጠጅ | black<br>ጥቁር | white<br>ነጭ | pink<br>ሮዝ |

## የቀለማት ባህሪ

- ቢጫ፣ ሰማያዊ እና ቀይ መሠረታዊ ቀለማት በመባል ይታወቃሉ::




- መሠረታዊ ቀለማትን በተለያየ ደረጃ በማቀላቀል በርካታ ቀለማትን ማግኘት ይቻላል::

<u>ለምሣሌ</u>:-

ቢጫ + ቀይ = ብርቱካንማ
ቀይ + ሰማያዊ = ወይን ጠጅ
ሰማያዊ + ቢጫ = አረንጓዴ
ሰማያዊ + ቢጫ + ቀይ = ግራጫ




- ከቀለማት ዓይነት ጥቁርና ነጭ መሠረታዊ ቀለማትን በማቀላቀል የማይገኙ በመሆናቸው ልዩ ያደርጋቸዋል:: ይኸውም ጥቁር ማንኛውንም ቀለም ተቀብሎ የማያስቀር ወይም የማያንፀባርቅ ሲሆን ነጭ ግን በተቃራኒው ማንኛውንም ቀለም ተቀብሎ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ ነው::



# English - Amharic Dictionary for Children

# እንግሊዝኛ - አማርኛ መዝገበ-ቃላት ለልጆች

አዘጋጅ
ዳንኤል(አበባየሁ) ወርቁ

© Mega Publishing Enterprise, 2002
ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1994

☎ 50 44 70
50 44 98

✉ 413 ኮድ 1110
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ

# የዚህ መዝገበ–ቃላት አጠቃቀም

ይህ መጽሀፍ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በሙሉ እንዲጠቀሙበት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህ መጽሃፍ እንደ ንባብ መጽሃፍ, አልያም እንደ መዝገበ–ቃላት ሊያገለግል ይችላል።

ህፃናት ስእሉን በመመልከት እና ቃሉን በማንበብ ትርጉሙን በትክክል መረዳት ይችላሉ። የበለጠ ቃሉ የማይረሣ እንዲሆን በጣም ቀላል በሆነ ዓረፍተ ነገር የቃሉ አጠቃቀም የተገለፀ ሲሆን የዓረፍተ ነገሩ የአማርኛ ትርጉምም ተካትቷል።

ልጆቹ ስእሉቹን ለመስራት እንዲሞክሩ መገፋፋት ቃሉን በቀላሉ እንዳይረሱት ለማድረግ ይረዳል።

ልጆቹ ዓረፍተ ነገሮቹን አንብበው ከተረዱ በኋላ የራሳቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲሰሩ መገፋፋቱም ጠቃሚ ነው። ይህም የማንበብ ልምዳቸውና ቃላትን በአግባቡ የመጠቀም ልምዳቸው እንዲዳብር ይረዳቸዋል።

የእንግሊዝኛው ቃላት አነባበብ የተቀመጠው በብሪታንያ አነባበብ ሲሆን ልጆቹ የቃላቱን ትክክለኛ አነባበብ እንዲገነዘቡ ታስቦ የተደረገ ነው።

ይህ መዝገበ-ቃላት ልጆቹ አዘውትረው እንዲጠቀሙበት የተዘጋጀ ሲሆን ይህን ማድረጋቸውም የቃላት እውቀታቸውና ዓረፍተ ነገር የመስራት ችሎታቸው እንዲዳብር ይረዳቸዋል።

እንደ I, he, she, you they የመሣሠሉትን ቃላት በቀላሉ መግለጽ ስለሚያስቸግር ለብቻቸው በሰንጠረዥ መልክ ቀርበዋል።

የቀለማት አይነቶች የፊት ሽፋኑ የውስጥ ገጽ ላይ፣ በጀርባው ሽፋን የውስጥ ገጽ ላይ ደግሞ የሰውን አካል የሚያሣይ ምስል ተካቷል።

## ምስጋና

ይህን መጽሃፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለወይዘሪት ጃክሊል ሐይሉ፣ ለወይዘሪት ሂሩት አሰግድ፣ ለወይዘሪት ራሄል ዘውዱ ፣ ለሰአሊ ግዛቸው ከበደ፣ ለሰአሊ አገኘሁ እና ለሰአሊ ዳንኤል ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

እንዲሁም ለሜጋ አሣታሚ ድርጅት የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች በተለይ ለትምህርት ስራዎች መምሪያና ለምርትና ዲዛይን ክፍል ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

## ማስታወሻ

## ለልጄ ለአቶ ፎፊ ዳንኤል

When I talk about myself
**እኔ ስለራሴ ስናገር**

| | | | |
|---|---|---|---|
| **I** like chocolate. | My father loves **me.** | **My** name is Fofy. | That is **mine.** |
| **እኔ ቸኮሌት እወዳለሁ።** | **አባቴ እኔን ይወደኛል።** | **የእኔ ስም ፎፊ ነው።** | **ያ የእኔ ነው።** |

**I** (አይ) **እኔ**
**Me** (ሚ) **እኔን**
**My** (ማይ) **የእኔ**
**Mine** (ማይን) **የእኔ ነው።**

When I talk to someone
**እኔ ከሌላ ሰው ጋር ስነጋገር**

| | | | |
|---|---|---|---|
| **You** are tall. | Your father likes **you.** | **Your** name is Misho. | That is **yours** |
| **አንተ እረጅም ነህ።** | **አባትህ አንተን ይወድሀል።** | **የአንተ ስም ሚሾ ነው።** | **ያ የአንተ ነው።** |

**You** (ዩ) **አንተ**
**You** (ዩ) **አንተን**
**Your** (ዩ:) **የአንተ**
**Yours** (ዩ:ዝ) **የአንተ ነው።**

When I talk about a boy or a man
**እኔ ስለ ወንድ ልጅ ወይም ሰው ስናገር**

| | | | |
|---|---|---|---|
| **He** is tall | Fofy likes **him.** | **His** name is Yohanan. | That is **his.** |
| **እሱ እረጅም ነው።** | **ፎፊ ይወደዋል።** | **የእሱ ስም ዮሀናን ነው።** | **ያ የእሱ ነው።** |

**He** (ሂ) እሱ
**Him** (ሂም) እሱን
**His** (ሂዝ) የእሱ
**His** (ሂዝ) የእሱ ነው።

When I talk about a girl or a woman
እኔ ስለ ሴት ልጅ ወይም ሰው ስናገር

| | | | |
|---|---|---|---|
| **She** is pretty. | Fofy likes **her** | **Her** name is Hanna | That is **hers.** |
| እሷ ቆንጆ ናት። | ፎፊ ይወዳታል። | የእሷ ስም ሃና ነው። | ያ የእሷ ነው። |

**She** (ሺ) እሷ
**Her** (ኸ፡) እሷን
**Her** (ኸ፡) የእሷ
**Hers** (ኸ፡ዝ) የእሷ ነው።

When I talk about animals or things
እኔ ስለ እንስሳት ወይም ህይወት ስለሌላቸው ነገሮች ስናገር።

| | | |
|---|---|---|
| **It** is a big dog. | Fofy likes **it.** | That is **its** tail. |
| እሱ ትልቅ ውሻ ነው። | ፎፊ እሱን ይወደዋል። | ያ የእሱ ጭራ ነው። |

**It** (ኢት) እሱ (ለእቃ ወይም ለእንስሳ)
**It** (ኢት) እሱን
**Its** (ኢትስ) የእሱ ነው።

When I talk about myself and other people
እኔ ስለ ራሴና ስለ ሰዎች በአንድነት ስናገር

| | | | |
|---|---|---|---|
| We are happy. | Fofy likes **us.** | That is **our** house. | That is **ours.** |
| እኛ ደስተኞች ነን። | ፎፊ እኛን ይወደናል። | ያ የእኛ ቤት ነው። | ያ የእኛ ነው። |

**We** (ዊ) እኛ
**Us** (አስ) እኛን
**Our** (አወ:) የእኛ
**Ours** (አወ:ዝ) የእኛ ነው።

When I talk about a lot of people or a lot of things
እኔ ስለ ብዙ ነገሮች ወይም ሰዎች ስናገር

| | | | |
|---|---|---|---|
| They are many. | Fofy likes **them.** | That is **their** car. | That is **theirs.** |
| እነሱ ብዙ ናቸው። | ፎፊ እነሱን ይወዳቸዋል። | ያ የእነሱ መኪና ነው። | ያ የእነሱ ነው። |

**They** (ዘይ) እነሱ
**Them** (ዘም) እነሱን
**Their** (ዜየ:) የእነሱ
**Theirs** (ዜየ:ዝ) የእነሱ ነው።

# Numbers Weights and Measurements
# ቁጥሮች፥ ክብደትና መለኪያዎች

## Numbers / ቁጥሮች

| | | |
|---|---|---|
| 0 | zero | ዜሮ |
| 1 | one | አንድ |
| 2 | two | ሁለት |
| 3 | three | ሶስት |
| 4 | four | አራት |
| 5 | five | አምስት |
| 6 | six | ስድስት |
| 7 | seven | ሰባት |
| 8 | eight | ስምንት |
| 9 | nine | ዘጠኝ |
| 10 | ten | አስር |
| 11 | eleven | አስራ አንድ |
| 12 | twelve | አስራ ሁለት |
| 13 | thirteen | አስራ ሶስት |
| 14 | fourteen | አስራ አራት |
| 15 | fifteen | አስራ አምስት |
| 16 | sixteen | አስራ ስድስት |
| 17 | seventeen | አስራ ሰባት |
| 18 | eighteen | አስራ ስምንት |
| 19 | nineteen | አስራ ዘጠኝ |
| 20 | twenty | ሀያ |
| 21 | twenty-one | ሀያ አንድ |
| 30 | thirty | ሰላሣ |
| 40 | forty | አርባ |
| 50 | fifty | ሀምሣ |
| 60 | sixty | ስልሣ |
| 70 | seventy | ሰባ |
| 80 | eighty | ሰማንያ |
| 90 | ninety | ዘጠና |
| 100 | one hundred | መቶ |
| 500 | five hundred | አምስት መቶ |
| 621 | six hundred and twenty-one | ስድስት መቶ ሃያ አንድ |
| 1,000 | one thousand | ሺህ |
| 1,000,000 | a million | ሚሊዮን |
| 1st | first | አንደኛ |
| 2nd | second | ሁለተኛ |
| 3rd | third | ሶስተኛ |
| 4th | fourth | አራተኛ |
| 5th | fifth | አምስተኛ |
| 6th | sixth | ስድስተኛ |
| 7th | seventh | ሰባተኛ |
| 8th | eighth | ስምንተኛ |
| 9th | ninth | ዘጠነኛ |
| 10th | tenth | አስረኛ |
| 20th | twentieth | ሃያኛ |

## Weight/ ክብደት

| | | |
|---|---|---|
| 1,000 grams(gm) | = | 1 kilogram (kg) |
| 1,000 ግራም | = | 1 ኪሎግራም |

## Length/ርዝመት

| | | |
|---|---|---|
| 10 millimetres(mm) | = | 1 centimetre(cm) |
| 10 ሚሊ ሜትር | = | 1 ሴንቲሜትር |
| 100 centimetres | = | 1 metre (m) |
| 100 ሴንቲሜትር | = | 1ሜትር |
| 1,000 metres | = | 1 kilometre(km) |
| 1,000 ሜትር | = | 1 ኪሎሜትር |

## Liquids/ፈሳሽ

| | | |
|---|---|---|
| 1,000 millilitres (ml) | = | 1 litre(1) |
| 1,000 ሚሊ ሊትር | = | 1ሊትር |

## Time/የሰዓትና የጊዜ አቆጣጠር

| | | |
|---|---|---|
| 60 seconds | = | 1minute (min) |
| 60 ሰከንድ | = | 1 ደቂቃ |
| 60 minutes | = | 1 hour(hr) |
| 60 ደቂቃ | = | 1 ሰአት |
| 24 hours | = | 1 day |
| 24 ሰአት | = | 1 ቀን |
| 7 days | = | 1 week(wk) |
| 7 ቀን | = | 1 ሳምንት |
| 365 days | = | 1 year (yr) |
| 365 ቀን | = | 1 አመት |
| 12 months | = | 1 year |
| 12 ወራት | = | 1 አመት |
| 100 years | = | 1 century (c) |
| 100 አመት | = | 1 ዘመን |

## Days of the week / የሳምንቱ ቀናት

| | | | |
|---|---|---|---|
| Sunday, | Monday, | Tuesday, | Wednesday, |
| እሁድ | ሰኞ÷ | ማክሰኞ÷ | ረቡዕ÷ |
| Thursday, | Friday, | Saturday, | |
| ሐሙስ÷ | አርብ÷ | ቅዳሜ÷ | |

## Months of the year /የአመቱ ወራት

| | | | |
|---|---|---|---|
| January, | February, | March, | April, |
| ጥር÷ | የካቲት÷ | መጋቢት÷ | ሚያዝያ÷ |
| May, | June, | July | August, |
| ግንቦት÷ | ሰኔ÷ | ሐምሌ÷ | ነሐሴ ÷ |
| September | October, | November, | December |
| መስከረም÷ | ጥቅምት÷ | ህዳር ÷ | ታህሳስ |

# Aa

*A,a* (ኤይ)
1. የእንግሊዝኛ የመጀመሪያው ፊደል
2. አንድ
My sister has a cat.
እህቴ አንድ ድመት አላት።

*able* ('ኤይብል)
አንድ ነገርን ማድረግ መቻል
My sister is able to swim.
እህቴ መዋኘት ትችላለች።

*about* (ኧ'ባውት)
1. አካባቢ/ገደማ ልክ ቦታው ላይ ሳይሆን በጣም የቀረበ
His brother is about ten years old.
የወንድሙ ዕድሜ ወደ አስር አካባቢ ነው።
2. ስለ
He told me a story about a hare.
ስለ ወንድ ጥንቸል ታሪክ ነገረኝ።

*above* (ኧ'በቨ)
በላይ
The light is above his head.
መብራቱ ከጭንቅላቱ በላይ ነው።



*absent* ('አብሰንት)
ቀሪ/በቦታው የሌለ/ያልተገኘ
My sister is absent from school.
እህቴ ከትምህርት ቤት ቀርታለች።

*accept* (ኧክ'ሴፕት)
አንድ ስጦታን ወይም ግብዣን መቀበል
I accepted your gift.
ስጦታህን ተቀብያለሁ።

*accident* ('አክሲደንት)
አደጋ/ አንድ መጥፎ ነገር ሲያጋጥም ለምሳሌ በመኪና መገጨት
The old lady is hurt in the car accident.
አሮጊቷ በመኪና አደጋው ተጐዱ።



*ache* (ኤይክ)
ህመም
My mother had a headache all morning.
ጠዋት እናቴ እራስ ምታት አሟት ነበር።

*across* (ኧክሮስ)
ከአንድ ዳር ወደ ሌላ ማቋረጥ
They built a bridge across the river.
ወንዙን የሚያቋርጥ ድልድይ ሰሩ።



*act* (አክት)
1. ትያትር መስራት

***A, a*** (ኤይ)
1. የእንግሊዝኛ የመጀመሪያው ፊደል
2. አንድ
My sister has a cat.
እህቴ አንድ ድመት አላት።

***able*** (ኤይብል)
አንድ ነገርን ማድረግ መቻል
My sister is able to swim.
እህቴ መዋኘት [redacted]

***about*** (ኧ'ባውት)
1. አካባቢ/ገደማ ልክ በቦታው ላይ ሳይሆን በጣም የቀረበ
His brother is about ten years old.
የወንድሙ ዕድሜ ወደ አስር [redacted] ነው።
2. ስለ
He told me a story about a hare.
ስለ ወንድ ጥንቸል ታሪክ ነገረኝ።

***above*** (ኧ'በቭ)
በላይ
The light is above his head.
መብራቱ ከጭንቅላቱ በላይ ነው።



***absent*** ('አብሰንት)
ቀሪ/በቦታው የሌለ/ያልተገኘ
My sister is absent from school.
እህቴ ከትምህርት ቤት ቀርታለች።


[illegible] (ኧክ'ሴፕት)
አንድ ስጦታን ወይም ግብዣን መቀበል
I accepted your gift.
ስጦታህን ተቀብያለሁ።

[illegible] ('አክሲደንት)
አደጋ/ አንድ መጥፎ ነገር ሲያጋጥም ለምሳሌ በመኪና መገጨት
The old lady is hurt in the car accident.
አሮጊቷ በመኪና አደጋው ተጎዱ።



[redacted] (ኤይክ)
ህመም
My mother had a headache all morning.
ጠዋት እናቴ እራስ [redacted] አሟት ነበር።

[illegible] (ኧክሮስ)
ከአንድ ዳር ወደ ሌላ ማቋረጥ
They built a bridge across the river.
ወንዙን የሚያቋርጥ ድልድይ ሰሩ።



***act*** (አክት)
1. ትያትር መስራት

My brother is acting in the school play.
ወንድሜ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ትያትር ይሰራል።
2. አንድ ነገር ማድረግ
You must act quickly to save his life.
ህይወቱን ለማዳን ፈጥነሽ አንድ ነገር ማድረግ አለብሽ።

*add* (አድ)
ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ነገሮችን መደመር
If you add four and three you will get seven.
አራትና ሶስትን ስትደምር ሰባት ታገኛለህ።

*address* (ኧ'ድሬስ)
አድራሻ/የሚኖሩበት ወይም የሚሰሩበት ቦታ
My address is in Addisu Kera.
አድራሻዬ አዲሱ ቄራ ነው።

*adjective* (አጀክቲቭ)
ቅጽል/ አንድን ነገር የበለጠ ለመግለጽ የሚጨመር
"Brave" is an adjective word.
"ጎበዝ" የሚለው ቃል ቅፅል ነው።

*adult* ('አደልት)
ትልቅ ሰው/ ጎልማሳ
My mother and father are adults.
እናቴና አባቴ ትልልቅ ሰዎች ናቸው።

*adventure* (ኧድ'ቬንቸ)
የሚያስደንቅ/የሚያስደስት ድርጊት
Going to a countryside is a great adventure.
ወደ ገጠር መሄድ በጣም አስደሳች ነገር ነው።

*advertisement* (ኧድ'ቨ፡ቲስመንት)
ስለ አንድ ነገር ወይም እቃ ጥሩነት የሚነገር የሚፃፍ ማስታወቂያ
Nowadays there are so many advertisements on TV.
በአሁኑ ጊዜ ብዙ ማስታወቂያዎች በቴሌቪዥን ይቀርባሉ።




*aeroplane* ('ኤየረፕሌይን)
የሚበር በአየር ላይ የሚሄድ ማሽን
Aeroplane carries people around the world.
አይሮፕላኖ ሰዎችን በአለም ዙሪያ ያመላልሣል።




*afraid* (ኧ'ፍሬይድ)
መፍራት
I am afraid of snakes and spiders.
እኔ ሸረሪትና እባብ እፈራለሁ።

*after* ('አ፡ፍተ)
1. ከኋላ
The lion's tail comes after its body.
የአንበሳ ጭራ ከሠውነቱ በኋላ ነው ያለው።
2.ቀይታ/ከአንድ ነገር በኋላ

I will see you after tea.
ከሻይ በኋላ እንገናኝ።

*afternoon* (ኢፍተ'ኑን)
ከሰአት/ ከቀኑ 6 ሰአት በኋላ ያለው ጊዜ
I will come at 1 o'clock in the afternoon.
ከሰአት በ7 ሰአት እመጣለሁ።

*again* (አ'ጌን)
እንደገና/በድጋሚ
Do not do it again.
እንደገና እንዳታደርገው።

*age* (ኤይጅ)
እድሜ
Are you twelve years of age?
አስራ ሁለት አመትህ ነው?

*ago* (አ'ገው)
ያለፈ ጊዜ ወይም ድሮ ከብዙ አመት በፊት
Dinosaurs lived many years ago.
ዳይኖሰርስ ከብዙ አመታት በፊት ይኖሩ ነበር።

*agree* (አ'ግሪ)
እሺ ማለት/ መስማማት
I agree to go to the library with you.
ከአንተ ጋር ወደ ቤተ- መጻህፍት ለመሄድ ተስማምቻለሁ።

*aim* (ኤይም)
1. ማነጣጠር
He aimed his gun at the antelope..
ድኩላዋ ላይ ጠመንጃውን አነጣጠረ።
2. አላማ/ የወደፊት እቅድ
Benti's aim is to be a great man.
የበንቲ አላማ ታላቅ ሰው መሆን ነው።

*air* (ኤየ)
አየር
To live, we need to breathe air.
ለመኖር አየር ያስፈልገናል።

*airport* ('ኤየፖ:ት)
የአይሮፕላን ማረፊያ
I am going to the airport to meet my father.
አባቴን ለመቀበል ወደ አይሮፕላን ማረፊያ እሄዳለሁ።

*alight* (አ'ላይት)
በእሣት መያያዝ/ መቃጠል
The match stick kept the fire alight.
የክብሪት እንጨቱ እሣቱን እንዳይጠፋ አደረገው።



*alive* (አ'ላይቭ)
በህይወት መኖር
My grandmother is alive.
አያቴ በህይወት አለች።

*all* (ኦ:ል)
[redacted] ሰው/ ሁሉም ነገር
All the elephants in the park are dead.
በፓርኩ ያሉ ዝሆኖች በሙሉ ሞተዋል።

*almost* ('ኦ:ልመውስት)
በአብዛኛው በጣም የቀረበ /የደረሰ/ ምንም ያልቀረው
Look ! It is almost four o'clock.
ተመልከት አራት ሰአት ሊሆን ምንም


አልቀረው።

***alone*** (ኧ'ለውን)
ለብቻ/ከሰው ተነጥሎ/
I was alone in the empty house.
በባዶ ቤት ውስጥ [illegible] ነበርኩ።

***along*** (ኧ:ሎን)
ከአንዱ ዳር እስከ ሌላው ዳር
He ran along the path to the house.
መንገዱን ተከትሎ ወደ ቤቱ ሮጠ።

***aloud*** (ኧ:ላውድ)
ጮክ ማለት/ድምጽን ከፍ ማድረግ
I want you to say the poem aloud.
ግጥሙን ጮክ ብለህ እንድታነብ እፈልጋለሁ።

***alphabet*** ('አልፈቤት)
ፊደል
*ሀ* is the first letter of the Amharic alphabet.
ሀ በአማርኛ የመጀመሪያ ፊደል ናት።



***also*** ('ኦ:ልሰው)
ደግሞ/ በተጨማሪ
Abebe was married and also his brother.
አበበ አግብቷል ወንድሙም ጭምር።


***altogether*** (ኦ:ልቶ'ጌዘ)
ሁሉንም ነገር በአንድነት/በጥቅሉ/
There are forty pupils in the class altogether.
በክፍሉ ውስጥ በጥቅሉ አርባ ተማሪዎች አሉ።

***always*** ('ኦ:ልዌይዝ)
ሁልጊዜ
The sun always sets in the west.
ፀሀይ ሁልጊዜ በምእራብ ትጠልቃለች።

***ambulance*** ('አምቢየለንስ)
አምቡላንስ/ሰዎች ሲታመሙ ወደ ሆስፒታል የሚወስድ መኪና
They put the lady with the broken leg in the ambulance.
እግራቸው የተሰበረውን ሴትዮ አምቡላንሱ ውስጥ አስገቧቸው።



***among*** (ኧመን)
ከሶስት በላይ ከሆኑ ነገሮች /ሰዎች መሀል
I found a square among the circles.
በክቦቹ መሀል አራት መአዘን አገኘሁ።



*amuse* (ኧ'ምዩ፡ዝ)
ሰውን ማሣቅ
The clown amused the children at the birthday party.
ኮሚኩ ሰው ህፃናቱን በልደት በአሉ ላይ አሣቃቸው።

*anchor* ('እንከ)
መልህቅ/ ትልቅ ብረት
መርከቦች አንድ ቦታ እንዲቆሙ የሚያደርግ/የመርከቦች ፍሬን/
All ships have an anchor.
ሁሉም መርከቦች መልህቅ አላቸው።



*angel* ('ኤይንጅል)
መልአክ/ የእግዚአብሔር መልእክተኛ
The angels brought the news to the shepherds.
መላእክቱ ዜናውን ለእረኞቹ አመጡላቸው።



*angle* ('እንግል)
መአዘን/ሁለት መስመሮች የሚገናኙበት ቦታ/አንግል/
How big are the angles in that square?
የካሬው መአዘኖች ምን ያህላሉ?



*angry* ('እንግሪ)
መቆጣት/ መናደድ
My mother was very angry.
እናቴ በጣም ተቆጥታ ነበር።

*animal* ('እኒመል)
እንስሳ/ህይወት ያለው የሚንቀሳቀስ ነገር በሙሉ
Dogs, horses, fishes, birds, butterflies and men are all types of animals.
ውሾች፣ ፈረሶች፣ አሣዎች፣ ወፎች፣ ቢራቢሮዎችና ሰዎች ሁሉም የእንስሣት አይነቶች ናቸው።



*ankle* ('እንክል)
ቁርጭምጭሚት/የእግርና የቅልጥም መገጣጠሚያ
My brother broke his ankle.
ወንድሜ ቁርጭምጭሚቱ ተሰበረ።



*another* (ኧ'ነዘ)
ሌላ/ካለው ተጨማሪ

Do you have another biscuit?
ሌላ ብስኩት አለህ?

***answer*** አ፡ንሰ)
ለጥያቄ የሚሰጥ መልስ
I don't have the answer for this question.
ለዚህ ጥያቄ መልስ የለኝም።

***ant*** (አንት)
ጉንዳን
Many ants live together in an anthill.
ብዙ ጉንዳኖች አብረው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ይኖራሉ።



***antelope*** ('አንቲለውፕ)
አጋዘን
There are antelopes in many parts of Africa.
በአፍሪካ በብዙ ቦታዎች አጋዘኖች ይገኛሉ።



***anybody*** ('ኤኒቦዲ)
ማንኛውም/ማንም ሰው
Can anyone lend me a pencil?
ከናንተ እርሣስ ሊያውሰኝ የሚችል አለ?

***anything*** ('ኤኒቲን)
ምንም ነገር
I don't want to say anything
ምንም ነገር ማለት አልፈልግም።

***anywhere*** ('ኤኒዌየር)
የትም ቦታ
I cannot find my coat anywhere.
ኮቴን የትም ቦታ ፈልጌ ላገኘው አልቻልኩም።

***apple*** ('አፕል)
1. ፖም 2. የሚበላ ፍሬ
I love to eat apple.
ፖም መብላት እወዳለሁ።



***approach*** (ኧፕረውች)
1. አቀራረብ 2. መገመት
It is dangerous to approach wild animals.
የዱር አራዊትን መቅረብ አደገኛ ነው።

***April*** (ኤይፕረል)
ሚያዝያ/ በጎርጎርሳውያን የአመቱ 4ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 8ኛ ወር
April comes after March.
ሚያዝያ ከመጋቢት ቀጥሎ ይመጣል።

***apron*** ('ኤይፕረን)
ሽርጥ/ ስራ ሲሠራ ልብስ እንዳይቆሽሽ ወገብ ላይና አንገት ላይ የሚታሠር ጨርቅ
My mother always wears an apron when she is cooking.
እናቴ ሁልጊዜ ምግብ ስትሰራ ሽርጥ ታስራለች።



***are*** (አ:)
የመሆን ግስ
We are, they are, you are.
እኛ ነን፣ እነሱ ናቸው፣ አንተ ነህ/ አንቺ ነሽ/እናንተ ናችሁ።

***arithmetic*** (ኧ'ሪትሜቲክ)
የቁጥር ትምህርት/ስራ/ አሪትሜቲክ
We can add, divide and multiply in arithmetic.
በቁጥር ትምህርት መደመር፣ ማካፈልና ማባዛት እንችላለን።

***ark*** (አ:ክ)
መርከብ
The ark saved Noah and his family from the flood.
ኖህና ቤተሰቦቹ ከጎርፍ ጥፋት የዳኑት በመርከብ ነው።



***arm*** (አ:ም)
ክንድ/ ከትከሻ እስከ መዳፍ ያለው አካል
Use both arms to pick up the box.
ሳጥኑን ለማንሣት ሁለቱንም ክንዶችህን ተጠቀም።




***army*** ('አ:ሚ)
ለውጊያ የሰለጠኑ ሰዎች/ ሠራዊት/ ጦር
Soldiers in the army use tanks and guns.
በሰራዊቱ ውስጥ ያሉት ወታደሮች ታንኮችንና ጠመንጃዎችን ይጠቀማሉ።

***around*** (ኧራውንድ)
ዙርያ
There is a line around the rooster.
በዶሮው ዙርያ መስመር አለ።



***arrive*** (ኧ'ራይቭ)
ጉዞ መጨረሻ መድረስ
We hope to arrive home at eight o'clock.
በሁለት ሰአት እቤት እንደርሳለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

***arrow*** (አረው)
ፍላፃ/ሜፉ ቀጭን ሹል የሚስፈነጠር/ ቀስት
The hunter shot the antelope with a poisoned arrow.
አዳኙ ድኩላዋን በመርዘኛ ፍላፃ ወጋት።



*ash* (አ'ሽ)
አመድ/ አንድ ነገር ከተቃጠለ በኋላ የሚቀረው ነጭ ብናኝ
The wind blew the ash from the fire all over the house.
ንፋሱ ከእሳቱ ላይ አመዱን በቤቱ ውስጥ አበነነው።

*asleep* (ኧ'ስሊ፡'ፕ)
መተኛት
The cat is asleep in front of the fire.
ድመቷ ከእሣቱ ፊት ለፊት ተኝታለች።

*assembly* (ኧ'ሴምብሊ)
ስብሰባ/ አንድ ነገር ለማድረግ የተሰበሰቡ ሰዎች
We sang a song at morning assembly.
በጠዋቱ ስብሰባ መዝሙር ዘመርን።



*athlete* ('አትሊ፡ት)
ሩጫ፥ ዝላይ ወይም የውርወራ ስፖርቶች የሚወዳደር ሰው
Haile Gebresilasie and Derartu Tulu are the best athlets.
ሀይሌ ገብረስላሴና ደራርቱ ቱሉ ምርጥ አትሌቶች ናቸው።



*atlas* ('አትለስ)
የአለም አገሮች ካርታ ያለበት መፅሃፍ
An atlas helps you to learn the countries of the world.
አትላስ የአለምን አገሮች እንድታውቅ ይረዳሃል።




*audience*(ኦዲየንስ)
ዘፈን ወይም ትያትር ለማየት የተሰበሰቡ ሰዎች
The audience is listening to her song quitely.
ተመልካቹ ዘፈኗን በፀጥታ እያዳመጠ ነው።



***August*** ('ኦ:ገስት)
ነሐሴ/ በጎርጎርሣውያን የአመቱ 8ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 12ኛ ወር
September comes after August.
ከነሀሴ ቀጥሎ መስከረም ይመጣል።

***aunt*** (አ:ንት)
አክስት/የእናት ወይም የአባት እህት/
My aunt gave me a gift on my birthday.
አክስቴ ለልደቴ ስጦታ ሰጠችኝ።

***author*** ('ኦ:ተ)
ደራሲ/መጽሃፍ የሚፅፍ ሰው/
I do not know the author of this book.
የዚህን መጽሃፍ ደራሲ አላውቀውም።

***autumn*** ('ኦ:ተም)
በልግ/ከበጋና ከረምት መሀል የሚመጣ የአመቱ ወቅት
During autumn, there is a lot of harvest in Ethiopia.
በበልግ ወቅት በኢትዮጲያ በርከት ያለ የእህል ምርት አለ።

***awake*** ('ኧ'ዌክ)
መንቃት/እንቅልፍ አለመተኛት
I was awake all night with a headache.
ሌሊቱን ሙሉ ራስ ምታት ስላመመኝ አልተኛሁም።

***away*** ('ኧ'ዌይ)
ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ያለው የቦታ ርቀት
My uncle's house is five kilometres away from our house.
የአጎቴ ቤት ከኛ ቤት አምስት ኪሎሜትር ይርቃል።

***axe*** ('አክስ)
መጥረቢያ/የእንጨት መቁረጫ መፍለጫ መሣሪያ
You need a sharp axe for cutting wood.
እንጨት ለመቁረጥ ስለታም መጥረቢያ ያስፈልግሃል።



*Bb* (ቢ:)
ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ፊደላት ሁለተኛው ፊደል

*baby* ('ቤይቢ)
ህፃን/በጣም ትንሽ [illegible]/
The baby is playing alone
ህፃኑ ብቻውን እየተጫወተ ነው።



*back* (ባክ)
ጀርባ፣ ከአንገት እስከ ቂጥ ያለው የሰውነት ክፍል
The baby is riding on the lion's back.
ህፃኑ በአንበሳው ጀርባ ላይ እየጋለበ ነው።



*backwards* ('ባክወድዝ)
በተቃራኒ አቅጣጫ መሄድ ወይም ወደ ኋላ መሄድ/ማንበብ
If you spell DAM backwards you get MAD.
DAM የሚለውን ወደ ሁዋላ ከነበብከው MAD የሚል ቃል ታገኛለህ።

*bad* (ባድ)
መጥፎ፣ ጥሩ ያልሆነ
Thief is a bad man.
ሌባ መጥፎ ሰው ነው።

*bag* (ባግ)
ከረጢት፣ ቦርሳ/ከወረቀት/ከጨርቅ ወይም ከፕላስቲክ የተሠራ እቃ መያዣ
Look! all these are bags.
ተመልከት እነዚህ ሁሉ ቦርሳዎች ናቸው።



*bake* (ቤይክ)
እንጀራ፣ዳቦ ወይም ኬክ መጋገር
My father is baking a cake for my birthday.
አባቴ ለልደቴ ኬክ እየጋገረልኝ ነው።



*alance* ('ባለንስ)
1. አንድ ነገር እንዳይወድቅ ማድረግ ሚዛኑን በመጠበቅ

The boy balanced the ball on his head.
ልጁ ኳሱን ራሱ ላይ ሚዛኑን ጠብቆ አቁሞታል።



2. ሚዛን/የእቃ ወይም የሰው ክብደት መለኪያ
Use the balance to weigh your weight.
ክብደትህን ለመለካት ሚዛኑን ተጠቀም።



*bald* (ቦ:ልድ)
ፀጉር የሌለው ራስ/መላጣ
My uncle is bald.
አጎቴ መላጣ ነው።

*ball* (ቦ:ል)
ኳስ ወይም ክብ የሆነ ነገር ሁሉ
They were playing with their new ball.
በአዲሱ ኳሳቸው እየተጫወቱ ነበር።



*balloon* (በ'ሉ:ን)
ፊኛ/በአየር የተሞላ የላስቲክ ከረጢት/
The boy blew up the balloons.
ልጁ ፊኛዎች ነፋ።



*banana* (በ'ና:ና)



The boy ate  banana for lunch.
ልጁ ለምሳው ሙዝ በላ።



*band* (ባንድ)
1. መቀነት/በአንድ ነገር ዙሪያ የሚታሰር ነገር/
My mother's hat has a green band

around it.
የእናቴ ኮፍያ አረንጓዴ መቀነት አለው።



2. አብረው ሙዚቃ የሚጫወቱ ሰዎች
The band is playing and the children are dancing.
ሙዚቀኞቹ ይጫወታሉ ልጆቹ ይደንሳሉ።



***bandage*** ('ባንዲጅ)
ቁሻ ቁስል የሚታሰርበት/ የሚጠቀለልበት ጨርቅ
The doctor put a bandage around the boy's head.
ሃኪሚ የልጁ ራስ ላይ ፋሻ አሰረችለት።



***bang*** (ባን)
ከፍተኛ ጩኸት ወይም ጋጋታ
The door closed with a bang.
በሩ በሃይል ጮሆ ተዘጋ።

***bank*** (ባንክ)
1. ከወንዝ ዳር ያለ ቦታ
We watched the fish from thc bank of the river.
ከወንዙ ዳር ሆነን አሳዎቹን ተመለከትን።



2. ገንዘብ ማስቀመጫ/ ማጠራቀሚያ
I keep my money in a bank.
ገንዘቤን ባንክ አስቀምጣለሁ።



***bar*** (ባ://ር)
ዱላ/ከብረት ወይ ከእንጨት የተሠራ ጠፍጣፋ
The bars on the lion's cage are very thick.
በአንበሣው ቤት ላይ ያሉት ጠፍጣፋ ብረቶች በጣም ወፍራሞች ናቸው።




***bare*** (ቤየ)
እርቃን/እራቁት ምንም ልብስ ያልለበሰ/
The boy is bare to his waist.
ልጁ እስከ ወገቡ ድረስ ራቁቱን ነው።

***bark*** ('ባ:ክ)
1. የውሻ ጩኸት
The dog barked at the birds on the tree.
ውሻው ዛፍ ላይ ባሉት ወፎች ላይ ጮኸባቸው።
2. ሽፋን/ልጥ
The tree has a smooth bark.
ዛፉ ለስላሳ ሽፋን/ልጥ አለው።


***barrel*** ('ባሬል)
1. ክብ በርሜል ስሩና ላዩ ጠፍጣፋ የሆነ ከእንጨት ወይም ከብረት የሚሠራ
The barrel is full of beer.
በርሜሉ በቢራ የተሞላ ነው።



***basin*** ('ቤይስን)
ገንዳ/ትልቅ ጎድጓዳ ነገር ውሃ የሚይዝ/ ለምሣሌ የእቃ ማጠቢያ/ የገላ መታጠቢያ
He washed his body in the basin.
ሰውነቱን በገንዳው ውስጥ ታጠበ።




***basket*** ('ባ:ስኬት)
ቅርጫት/ሙዳይ /ከሣጠራ ወይም ከቀርከሃ የሚሰራ እቃ መደገፊ
A basket is made up of grass.
ቅርጫት ከሳር ይሰራል።



***bat*** (ባት)
የሌሊት ወፍ/አይጥ የሚመስል መልክ ያላት ሲመሽ ብቻ የምትበር እንስሳ
Bats like to fly at night.
የሌሊት ወፎች በምሽት መብረር ይወዳሉ።



***bath*** (ባ'ስ)
የገላ መታጠቢያ ገንዳ/ትልቅ
He told the dirty boy to get into the bath.
የቆሸሸውን ልጅ ገንዳው ውስጥ ገብቶ እንዲታጠብ ነገረው።



***bathroom*** ('ባ:ስሩም) ስ-
የሰውነት መታጠቢያ ክፍል
My mother is in the bathroom.
እናቴ በመታጠቢያ ቤት ውስጥ ነች።

***battery*** ('ባትሪ)
ባትሪ/ የኤሌክትሪክ ሃይል የሚያመነጭ ትንሽ ክብ ድንጋይ/ ለሬዲዮ፣ ለቴፕ ማጫወቻነት የሚያገለግል።
የተለያዩ ባትሪዎች አሉ።
My brother bought a new battery for his radio.
ወንድሜ ለሬዲዮው አዲስ ባትሪ ገዛ።



This is a video camera battery.
ይሄ የቪዲዮ ማንሻ ካሜራዎች ባትሪ ነው።




This is a car battery.
ይሄ የመኪና ባትሪ ነው።



***be*** (ቢ:)
የአንድ ነገር ምንነትን አመልካች ግስ /ነው/
I want to be a nurse.
ነርስ መሆን እፈልጋለሁ።

***beak*** (ቢ:ክ)
መንቁር/የወፎች/የዶሮዎች ጠንካራው የአፋቸው ክፍል/
All birds have a hard beak.
ወፎች ሁሉ ጠንካራ መንቁር አላቸው።



***bean*** (ቢ:ን)
ባቄላ/ውስጡ ትላልቅ ፍሬዎች ያሉት አረንጓዴ ተክል/
My mother cooked the beans for supper.
እናቴ ለመክሰስ ባቄላ ቀቀለች።



***bear*** (ቤይ)
ድብ/የዱር እውሬ/
A bear likes to eat rats.
ድብ አይጦችን መብላት ይወዳል።



***beard*** (ቢየድ)
ጺም/ወንድ ልጅ 18 አመት ከሞላው በኋላ በአገጭና ጉንጭ አካባቢ የሚበቅል ፀጉር
The old man has a long beard.

ሽማግሌው ረጅም ፂም አላቸው።




*beast* (ቢ:ስት)
አውሬ/የዱር አውሬ/ለሃምሳሌ አንበሳ፣ ነብር የመሳሰሉ
We heard the cry of a wild beast from the woods.
ከጫካው ውስጥ የአውሬ ጩኸት ሰማን።

*beat* (ቢ:ት)
በአለንጋ /በልምጭ መግረፍ
The man beat the boy with a stick.
ሰውየው ልጁን በልምጭ ገረፈው።

*beautiful* ('ብዩ:ተፍል)
ቆንጆ፣ የሚያምር
She is very beautiful.
በጣም ቆንጆ ነች።

*because* (ቢ:ይኮዝ)
ምክንያቱም
I ran home because it was going to rain.
ዝናብ ሊዘንብ ሲል ወደ ቤት እየሮጥኩ ሄድኩ።

*bed* (ቤድ)
አልጋ/አራት እግሮች ያሉት ሰፊ ሆኖ ለመኝታ የሚያገለግል
Lie on the bed and sleep.
አልጋ ላይ ውጣና ተኛ።



*bedroom* ('ቤድ:ሩ:ም)
መኝታ ቤት
My bedroom is very small but I love it.
መኝታ ቤቴ በጣም ጠባብ ናት ግን እወዳታለሁ።

*bee* (ቢ:)
ንብ/ማር የምትሠራ ትንሽ ነፍሳት/
There are bees in that tree.
እዛ ዛፍ ላይ ንቦች አሉ።



*beef* (ቢ:ፍ)
የበሬ ወይም የላም ስጋ
The beef was cut up to be cooked.
ሥጋው ለወጥ ተከትፎ ተዘጋጅቷል።

*before* (ቢ'ፎ:)
በፊት
Sunday comes before Monday.
እሁድ ከሰኞ በፊት ይመጣል።

*begin* (ቢ'ጊን)
አንድን ነገር መስራት መጀመር
My mother asked me to begin digging the garden.
እናቴ የአትክልቱን ቦታ መቆፈር እንድጀምር ነገረችኝ።

***behind*** (ቢ'ሃይንድ)
ከአንድ ነገር ሁዋላ/ከጀርባ
The puppy hid behind its mother.
ቡችላው ከእናቱ ሁዋላ ተደበቀ።

***bell*** (ቤል)
ደወል/ቃጭል ከብረት የተሠራ ከውስጡ የሚወዛወዝ ብረት ያለው ሲወዘውዙት እየተጋጨ የሚጮህ/የሚደውል/ በኤሌክትሪክ የሚሠራም አለ
The teacher rang the school bell.
መምህሩ የትምህርት ቤቱን ደወል ደወሉ።




***belong*** (ቢ'ሎንግ)
1. የአንድ ሰው ንብረት
That pencil belongs to me.
ያ እርሳስ የኔ ነው።
2. የአንድ ነገር አካል/አባል
Do you belong to the football team?
አንተ የእግር ኳስ ቡድኑ አባል ነህ?

***below*** (ቢ'ለው)
በታች/ከአንድ ነገር ስር/
The snake slid below the stone.
እባቡ በድንጋዩ ስር ሾለከ።

***belt*** (ቤልት)
ቀበቶ፣ ወገብ ላይ የሚታሰር ከቆዳ/ከጨርቅ፣ ከላስቲክ የሚሠራ
The man wore a belt.
ሰውየው ቀበቶ ታጥቋል።




***bench*** (ቤንች)
አግዳሚ ወንበር/ከእንጨት/ከድንጋይ የሚሠራ ከሁለት በላይ ሰው የሚያስቀምጥ
The three children sat on the bench.
ሶስቱ ልጆች አግዳሚ ወንበሩ ላይ ተቀመጡ።



***bend*** (ቤንድ)
1. የመኪና መንገድ መታጠፊያ
The bus drove round the bend too fast.
አውቶብሱ መታጠፊያው ላይ በጣም ፈጠነ።



2. የጎበጠ ነገር
That book is bend.
ያ መጽሃፍ ታጥፏል።



***beneath*** (ቢ'ኒ፡ስ)
ከስር/ከአንድ ነገር ስር
The boat sailed beneath the bridge.
ጀልባው በድልድዩ ስር አለፈ።

***berry*** ('ቤሪ)
እንጆሪ
The birds ate all the berries.
ወፎቹ ሁሉንም እንጆሪዎች በሉዋቸው።


***beside***(s) (ቢ' ሳይድ(ዝ)
አጠገብ/ከአንድ ነገር አጠገብ
The dog is sitting beside the cat.
ውሻው ከድመቷ አጠገብ ተቀምጧል።



***best*** (ቤስት)
ከሁሉ የተሻለ/የበለጠ
He is the best footballer in the class.
በክፍሉ ውስጥ ካሉት ሁሉ የበለጠ ኳስ ተጫዋች ነው።

***better*** ('ቤተ)
የበለጠ/ ከሌላው የተሻለ
Bekele's cake is better than Sarah's.
የበቀለ ኬክ ከሳራ የተሻለ ነው።

***between*** (ቢ' ትዊ፡ን)
ከሁለት ነገሮች መሀከል
The boy sat between his mother and his father.
ልጁ ከአባቱና ከእናቱ መሃል ተቀመጠ።



***beyond*** (ቢ' ዮንድ)
አልፎ እርቆ መሄድ
The ball went beyond the goal
ኳሱ ከጎሉ አልፎ ሄደ።

***Bible*** ('ባይብል)
መጽሐፍ ቅዱስ/የክርስቲያኖች ቅዱስ መጽሃፍ
Kumsa reads the Bible every night.
ኩምሳ ዘወትር ማታ ማታ መጽሀፍ ቅዱስ ያነባል።

***bicycle*** ('ባይሲክል)
ብስክሌት/ ባለ ሁለት ጎማ ተሽከርካሪ
Tewelde rides his bicycle to school everyday.
ተወልደ በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤቱ በብስክሌት ይሄዳል።



*big* (ቢግ)
ትልቅ
The rabit has big ears.
ጥንቸሏ ትልልቅ ጆሮዎች አሏት።



*bill* (ቢል)
የገዙት ነገር ዋጋው የተፃፈበት ወረቀት
Mamo paid the bill for the chicken he bought.
ማሞ ለገዛው ዶሮ በዋጋ መጠይቁ መሠረት ከፈለ።

*bin* (ቢን)
ትልቅ ጎድጓዳ ከቆርቆሮ ወይም ከፕላስቲክ የተሰራ ለሃን ለእህል/ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ
Please put those old tins in the bin.
እባክህ እነዛን አሮጌ ጣሳዎች ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ክተታቸው።



*bird* (በ:ድ)
ወፍ/የመብረሪያ ክንፍ ያላት በላባ የተሸፈነችና ጠንካራ አፍ ያላት እንስሣ
The bird flew high into the sky.
ወፏ በሰማይ ላይ ርቃ በረረች።



*birth* (በ:ዝ)
መውለድ
The cat gave birth to five kittens.
ድመቷ አምስት ግልገሎች ወለደች።

*biscuit* ('ቢስኪት)
ብስኩት
Semira had two biscuits with her tea.
ሰሚራ ሁለት ብስኩቶች በሻይዋ በላች ።

*bit* (ቢት)
ትንሽ/ቁራጭ ወይም ቁራሽ
Mimi ate a small bit of the cake.
ሚሚ ቁራጭ ኬክ በላች።

*bite* (ባይት)
መግመጥ/ መንከስ
She bite into the apple.
ፖሙን ገመጠችው።

*black* (-ብላክ)
1. ጥቁር
I have a black shoes.
ጥቁር ጫማ አለኝ።
2. ጨለማ/ብርሃን የሌለው
The night is black.
ምሽቱ ጨለማ ነው።



*blackboard* ('ብላክቦ፡ድ) ስ-
ጥቁር ሰሌዳ
The teacher is writing a question on the blackboard.
አስተማሪው ጥቁር ሠሌዳው ላይ ጥያቄ እየፃፈ ነው።

*blade* (ብሌይድ) ስ-
ምላጭ/ ስስና ጠፍጣፋ ስለታም ነገር
Don't touch the blade you will cut your finger.
ምላጩን አትንካ ጣትህን ይቆርጥሃል።

*blanket* ('ብላንኪት)
ብርድልብስ
In winter I need three blankets on my bed.
በክረምት ለመኝታዬ ሶስት ብርድልብሶች ያስፈልጉኛል።

*bleed* (ብሊ፡ድ)
የደም መፍሰስ
His nose began to bleed.
ከአፍንጫው ደም መፍሰስ ጀመረ።

*blind* (ብላይንድ)
አይኖቹ የማያዩ/አይነ ስውር
The boy helped the blind man to cross the road.
ልጁ አየነ ስውሩን ሰው መንገዱን እንዲያቋርጥ ረዳው።

*blink* (ብሊንክ)
አይንን ቶሎ ቶሎ እየከፈቱ መጨፈን/ መጥቀስ
My mother used to blink as she chop the  onion.
እናቴ ሽንኩርት ስትከትፍ አይኖቿን ቶሎ ቶሎ ትዘጋና ትከፍት ነበር።

*blood* (ብለድ)
ደም/ሰውነት ሲቆረጥ የሚፈስ ቀይ ፈሣሽ
The girl cried when she saw blood on her finger.
ልጅቷ እጇ ላይ ደም ስታይ ጮኸች።

*blow* (ብለው)
1. በሀይል መምታት
The boy fell with the first blow.
ልጁ በመጀመሪያው ምት ወደቀ።
2. እፍ ማለት/በሃይል መተንፈስ
I will blow out the candle.
ሻማውን እፍ ብዬ አጠፋዋለሁ።



*blue* (ብሉ)
ሰማያዊ
My mother wore a blue hat.
እናቴ ሰማያዊ ባርኔጣ አድርጋለች።

*blunt* (ብለንት)
የደነዘ/ስለት የሌለው
The blunt  knife can not cut the meat.
የደነዘው ቢላዋ ስጋ ሊቆርጥ አይችልም።

*bourd* (ቦ:ድ)
ሰፊ ዝርግ እንጨት/ሰሌዳ
My father made a dama board with a piece of board.
አባቴ ከጠፍጣፋ እንጨት የዳማ መጫወቻ ሰራ።



*boat* ('በውት)
ጀልባ/ሰዎችን በውሃ ላይ የሚያመላልስ
They crossed the lake with the boat.
በጀልባ ሃይቁን አቋረጡ።



*body* ('ቦዲ)
ሰውነት
An exercise makes your body strong.
የአካል እንቅስቃሴ ሰውነትህን ያጠነክራል።



*boil* (ቦይል)
የፈላ ውሃ/ማፍላት
My father boiled the water for tea.
አባቴ ለሻይ ውሃውን አፈላ።

*bone* (በውን)
አጥንት
The dog is eating the bone.
ውሻው አጥንቱን እየበላ ነው።



*book* (ቡክ)
መፅሀፍ
My father is reading a book about cars.
አባቴ ስለመኪና የተፃፈ መጽሐፍ እያነበበ ነው።



*boot* (ቡ:ት)
1. ቦት ጫማ/እግርንና ቁርጭምጭሚትን የሚሸፍን ጫማ
She wears boots in winter.
በክረምት ቦት ጫማ ታደርጋለች።



2. የመኪና ኋላ ዕቃ ማስቀመጫ ቦታ

The girl put her bag in the boot of the car.
ልጅቷ ቦርሳዋን ከመኪናው ኋላ ባለው እቃ ማስቀመጫ ውስጥ አስቀመጠች፡



*born* (ቦ:ን)
መወለድ
I was born in September.
የተወለድኩት በመስከረም ነው።

*borrow* ('ቦረው)
ተጠቅሞ ለመመለስ መዋስ ወይም መበደር
Can I borrow your book?
መጽሀፍህን ልዋስ እችላለሁ?

*both* (በውስ)
ሁለቱም
Tolosa ate both oranges.
ቶሎሳ ሁለቱንም ብርቱካኖች በላ።

*bottle* ('ቦትል)
ከጠርሙስ/ከፕላስቲክ የሚሠራ ሾጣጣ የፈሳሽ መያዣ/ ጠርሙስ/ ጡጦ
She bought two bottles of milk for the baby.
ከሱቅ ሁለት ጠርሙስ ወተት ለህጻኑ ገዛች።




*bottom* ('ቦተም)
1. የአንድ ነገር የስረኛው ክፍል/ቂጥ
There is something at the bottom of the bottle.
ከጠርሙሱ ስር አንድ ነገር አለ።



2. የሰው መቀመጫ/ቂጥ
Kumssa hurt his bottom when he fell off the chair.
ኩምሳ ከወንበሩ ሲወድቅ ቂጡን አመመው።

*bounce* (ባውንስ)
መንጠር/ማንጠር
The ball bounced against the wall.
ኳሱ ግድግዳው ላይ ነጠረ።

*bow* (በው)
1. ቀስት/ደጋን ከጎባጣ እንጨትና ከጠንካራ ክር የሚሠራ የፍላፃ መወርወሪያ
He put an arrow into his bow.
ፍላፃውን በቀስቱ ላይ አደረገው።



2 ከረባትን/ገመድን የሚሜማ ክርን አጠላልፎ መቋጠር
Please tie the string in a bow.
የሚሜማ ክርህን አጠላልፈህ እሰረው።



*bowl* (በውል)
ትንሽ ገበቴ/ክብ ጎድጓዳ ሰሃን
My mother put the bowl of fruit on the table.
እናቴ በጉድጓዳ ሰሀን ፍራፍሬ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠች።



*box* (ቦክስ)
1. ሳጥን/ ከእንጨት ወይም ከብረት የሚሰራ እቃ ማስቀመጫ
My mother puts her clothes in a golden box.
እናቴ ልብሶቿን በወርቃማ ሳጥን ውስጥ ታስቀምጣለች።
2. እጅን ጨብጦ በቡጢ መደባደብ
How can you box with your friend?
እንዴት ከጓደኛህ ጋር በቡጢ ትደባደባለህ?

*boy* (ቦይ)
~~ወንድ ልጅ~~
The boy climbed over the tree.
ልጁ ዛፉ ላይ ወጣ።



*brake* (ብሬይክ)
ፍሬን/የመኪና የብስክሌት የፍጥነት መቀነሻ/ማቆሚያ
Brake is an important part of a car.
ፍሬን የመኪና አስፈላጊ አካል ነው።

*branch* (ብራ፡ንች)
ቅርንጫፍ/ ከዛፍ ዋንኛ ግንድ ላይ የበቀለ
Many birds build their nests in the branches of trees.
ብዙ ወፎች በዛፍ ቅርንጫፎች ላይ ጎጆአቸውን ይሰራሉ።



*brave* (ብሬይቭ)
ጎበዝ/ደፋር/ የማይፈራ
Yonas is very brave. He helped the police to catch the thieves.
ዮናስ በጣም ጎበዝ ነው ፖሊሶቹ ሌቦቹን እንዲይዙ አገዛቸው።

*bread* (ብሬድ)
ዳቦ
Bread with tea is my favourite breakfast.
ዳቦ በሻይ በጣም የምወደው ቁርስ ነው።



*break* (ብሬክ)
መስበር/አንድን ነገር ለሁለት ወይ ከዛ በላይ መቁረጥ
I break a glass when I fill dizzy.
ድካም ሲጫጫነኝ ብርጭቆ እሰብራለሁ።

*breakfast* ('ብሬክፈስት)
ቁርስ/ በጠዋት የሚበላ ምግብ
I like egg for my breakfast.
ቁርሴን እንቁላል መብላት እወዳለሁ።




*breathe* (ብሪ:ዝ)
መተንፈስ/አየር በአፍ /በአፍንጫ/ መሣብና ማስወጣት
We cannot breathe under water.
በውሀ ውስጥ አየር መሣብ አንችልም።

*breeze* (ብሪ:ዝ)
ለስለስ ያለ ነፋስ
The breeze moved the leaves on the trees.
ለስለስ ያለው ነፋስ የዛፉን ቅጠሎች አወዛወዛቸው።

*brick* (ብሪክ)
ጡብ/ሸክላ/ከሸክላ አፈር ከሲሚንቶ የተሰራ አራት መአዘን ድንጋይ
They used red bricks to build the wall.
ግድግዳውን ለመስራት ቀይ ጡቦችን ተጠቀሙ።



*ride* (ብራይድ)
ሙሽራ/ የጋብቻ በዓሏን የምታከብር ሴት
The bride wore a long white dress on her wedding day.
ሙሽራዋ በሰርጓ እለት እረዥም ነጭ ቀሚስ ለበሰች።



*briage* (ብሪጅ)
ድልድይ/ወንዝን/ ለመሻገር የሚሠራ መንገድ
I watched boats going under the bridge.
በድልድዩ ስር ጀልባዎች ሲሄዱ አየሁ።



*bright* (ብራይት)
ብሩህ/ብዙ ብርሀን ያለው/ ደማቅ

It's bright day lets play.
ቀኑ ብሩህ ነው እንጫወት።

*bring* (ብሪንግ)
**አንድን ነገር ይዞ ማምጣት**
Tedi is bringing his friend to lunch on Saturday.
ቴዲ ጓደኛውን ቅዳሜ እለት ለምሳ ይዞት ይመጣል።

*broad* (ብሮ፡ድ)
**ሰፊ**
Ethiopia is a broad country.
ኢትዮጵያ ሰፊ አገር ናት።

*brooch* (ብረውች)
**ልብስ ላይ የሚለጠፍ ጌጥ**
She wore a red brooch on her dress.
ቀይ ጌጥ ልብሷ ላይ ለጥፋለች።

*broom* (ብሩ፡ም)
**መጥረጊያ**
The children took brooms and started to clean the floor.
ልጆቹ መጥረጊያ ወስደው ወለሉን መጥረግ ጀመሩ።



*brother* ('ብረዘ)
**ወንድም**
My brother is taller than I am.
ወንድሜ ከኔ ይረዝማል።

*brown* (ብራውን)
**ቡኒ/ ቡና አይነት ቀለም/ የሻይ ወይም የቸኮሌት ቀለም**
Tea leaves in a tea-cup are dark brown.
የሻይ ቅጠል በሻይ ስኒ ውስጥ ጥቁር ቡና አይነት ነው።

*bruise* (ብሩ፡ዝ)
**የበለዘ ቦታ/በቆዳ ላይ የጠቆረ ቦታ/**
Bilen fell off the chair and bruised her arm.
ብሌን ከወንበር ወድቃ እጇ በለዘ።

*brush* (ብረሽ)
**ቡሩሽ/አጭር ሀጉሮች ያሉት የፀጉር መቦረሻ/የጥርስ ቡሩሽ/ የቀለም ቡሩሽ**
My mother gave me a new tooth brush.
እናቴ አዲስ የጥርስ ቡሩሽ ሰጠችኝ።



*bubble* ('በብል)
**[illegible]**
My coke is full of bubbles.
ኮካዬ በአረፋ የተሞላ ነው።



***bucket*** (በኬት)
ባሊ/የፈላሽ መያዣ/ከብረት/ከፕላስቲክ የተሰራ ባለማንጠልጠያ
Alula filled his bucket with water.
አሉላ ባሊውን በውሃ ሞላው።



***bud*** (በድ)
እንቡጥ አበባ/ገና ማበብ የጀመረ አበባ
The caterpillar ate all the buds on the flower.
አባጨጓሬው እምቡጥ አበባውን በሙሉ በላው።



***build*** (ቢልድ)
መገንባት/መስራት አንድን ነገር ቀስ በቀስ ማሳደግ ከፍ ማድረግ
It took two years to build the house.
ቤቱን ለመገንባት ሁለት አመት ፈጀ።

***building*** (ቢልዲን)
ህንፃ /ቤት/ስራ የሚሠሩበት ወይም የሚኖሩበት ቦታ
My father's office is in that building.
የአባቴ ቢሮ በዚያ ሕንፃ ውስጥ ነው።



***bull*** (ቡል)
ወንድ የቀንድ ከብት/ኮርማ በሬ
Kassim's father has three bulls.
የቃሲም አባት ሦስት ኮርማዎች አሏቸው።



***bullet*** (ቡሊት)
ጥይት/ከሽጉጥ/ከጠመንጃ የምትተኮስ ቁራጭ ብረት
There are only two bullets left in the gun.
በጠመንጃው ውስጥ ሁለት ጥይቶች ብቻ ቀርተዋል።



***bump*** (በምፕ)
ያበጠ ነገር/ ሰውነት ወይም ቆዳ ላይ
The baby had a bump on her head where she fell.
ልጅቷ ስትወድቅ ጭንቅላቷ አበጠባት።

***bunch*** (በንች)
እኝጭ ላይ የታሰረ ነገር

He bought a bunch of flowers in the market.
አንድ ላይ የታሰሩ አበቦች ከገበያ ገዛ።



*burn* (በ፡ን)
**በእሳት ማያያዝ ወይም በእሳት ማቃጠል/ ማንደድ**
The dry wood burned very quickly.
ደረቁ እንጨት ቶሎ ነደደ።



*burst* (በ፡ስት)
[redacted]
The balloon burst in Misho's face.
ፊኛው ሚሾ ፊት ላይ ፈነዳ።

*bus* (በስ)
**[redacted]ልቅ መኪና፣ ባንዴ ብዙ ሰዎች የሚያሣፍር/**
The children travel to school by bus everyday.
ልጆቹ በየቀኑ በአውቶቡስ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ።



*bush* (ቡሽ)
**ቁጥቋጦ**
Bushes are short trees.
ቁጥቋጦዎች አጫጭር ዛፎች ናቸው።



*busy* (ቢዚ)
**በስራ የተጠመደ/ስራ የበዛበት ሰው/**
My father is busy in the garden.
አባቴ በአትክልት ቦታው ውስጥ በስራ ተጠምዷል።

*but* (በት)
**ነገርግን**
It is good but not beautiful.
ይሄ ጥሩ ነው ነገርግን ቆንጆ አይደለም።

*butcher* (ቡቸ)
**ስጋ ነጋዴ/ስጋ የሚሸጥ ሰው/**
Abebe bought a kilogram of meat from the butcher.
አበበ ከስጋ ነጋዴው አንድ ኪሎ ስጋ ገዛ።




*butter* ('በተ)
ቅቤ/ከወተት የሚገኝ ቢጫ ምግብ ማጣፈጫ
I like to eat bread and butter.
ዳቦ በቅቤ መብላት እወዳለሁ።

*butterfly* ('በተፍላይ)
ቢራቢሮ/ትልቅ ባለቀለም ክንፎች ያሏት ነፍሳት/
The butterfly has red and black wings.
ቢራቢሮዋ ቀይና ጥቁር ክንፎች አሏት።



*button* ('በትን)
ቁልፍ/ልብስ ላይ የሚሰፋ ትንሽ ክብ ነገር በቀዳዳ እየሾለከ/ልብስ የሚያያይዝ/
My mother sewed a button on my shirt.
እናቴ ሸሚዜ ላይ ቁልፍ ሰፋችልኝ።



*buy* (ባይ)
መግዛት
My uncle will buy me a bicycle for my birthday.
አጎቴ ለልደቴ ብስክሌት ይገዛልኛል።

*buzzard* ('በዘድ)
የሎስ/ትንንሽ እንስሳትን እየገደለ የሚበላ አሞራ
The buzzard carried the mouse back to its nest.
የሎሱ አይጧን አንጠልጥሎ ጎጆው ወሰዳት።



*by* ('ባይ)
በ
The cooker works by gas.
ምድጃው በጋዝ ይሰራል።
We will be there by six o'clock.
ልክ በስድስት ሰአት እዛ እንደርሳለን።


# Cc

*C,c* (ሲ፡)
የእንግሊዝኛ ሶስተኛው ፊደል

*cabbage* ('ካቢጅ)
ጥቅል ጎመን/የተደራረበ/ ክብ የሆነ ተክል
I do not like cabbage.
ጥቅል ጎመን አልወድም።



*cactus* ('ካክተስ)
ቁልቋል/ አረንጓዴ የሆነ ጥቃቅን እሾሆች ያሉት ተክል
A cactus needs very little watcr.
ቁልቋል ትንሽ ውሀ ነው የሚያስፈልገው።



*café* ('ካፌይ)
ቀላል ምግብና መጠጥ ተገዝቶ የሚበላበት ቦታ/ካፌ/
We stopped at the café for coffee and cakes.
ኬክና ቡና ለመግዛት ካፌው ጋ ቆምን።

*cage* (ኬይጅ)
ከብረት የተሰራ ቤት
The lion tried to escape from its cage.
አንበሳው ከብረት ቤቱ ለማምለጥ ሞከረ



*cake* (ኬይክ)
ኬክ/ ከእንቁላል፣ ከዱቄትና ከስኳር የሚሠራ ለስላሣ ጣፋጭ ዳቦ
I had a chocolate cake for my birthday.
ለልደቴ የቸኮሌት ኬክ ነበረኝ።




*calendar* ('ካሊንደ)
የቀን መቁጠሪያ
Mola crossed off the days on the calendar.
ሞላ በቀን መቁጠሪያው ላይ ያሉትን ቀናት ሰረዛቸው።



*calf* (ካ፡ፍ)
ጥጃ/የላም ልጅ
The calf followed its mother.

ጥጃው እናቱን ተከተለ።



2. ባት/የቅልጥም ጀርባ
Tolossa ran with a bandage round his calf.
ቶሎሣ ባቱ ላይ ፋሻ ጠቅልሎ ሮጠ።

*call* (ኮ:ል)
1. ጮሆ መጣራት
She called her sister when she saw her.
እህቷን ስታያት ጠራቻት።
2. ሰው መጎብኘት መጠየቅ
My father called his brother yesterday.
አባቴ ትላንትና ወንድሙን ጠየቀው።
3. የሚጠሩበት ስም
He is called Fofi.
እሱ ስሙ ፎፊ ይባላል።


*camel* ('ካምል)
ግመል/ትልቅ ከጀርባው ሁለት ወይም አንድ ያበጠ ነገር/ሻኛ/ ያለው እንስሣ/
Camels are used in very dry places.
ግመሎች በጣም ሞቃት በሆነ ቦታ ያገለግላሉ።



*camera* ('ካመረ)
1. የማይንቀሣቀስ ፎቶ ማንሻ
The boy took a photograph of his mother with his new camera.
ልጁ በአዲሱ ካሜራው እናቱን ፎቶ አነሣ።




2. /ተንቀሣቃሽ ፎቶ ፊልም ማንሻ/ ቪዲዮ/
The journalist has a video camera.
ጋዜጠኛው ተንቀሳቃሽ ፎቶ ፊልም ማንሻ አለው።



*camp* (ካምፕ)
ሰዎች ለአጭር ጊዜ በአንድነት

የሚኖሩበት ቦታ
They stayed at the camp for weekend.
ቅዳሜና እሁድ በካምፕ ውስጥ ቆዩ።

*can* (ካን)
1. ጣሳ፣ በቆርቆሮ የሚሠራ ፈሳሽ ወይም ዱቄት መያዣ
My father needs three cans of oil for the car.
አባቴ ለመኪናው ሶስት ጣሳ ዘይት ይፈልጋል።




2. መቻል/አንድ ነገር ማድረግ
I can read and write.
ማንበብና መፃፍ እችላለሁ።

*canal* (ከናል)
1. ሰው ቆፍሮ የሰራው ወንዝ ወይም ሰርጥ
The Suez Canal goes from the Mediterranean to the Red sea.
ስዊዝ ካናል ሜዲትራንያንንና ቀይ ባህርን ያገናኛል።
2. ስሮች/በሰውነት ውስጥ የምግብና የደም መዘዋወሪያ/



*candle* (ካንድል)
ሻማ/ከሰምና ክር የሚሠራ መብራት
We lit the candles when the lights went off.
መብራቱ ሲጠፉ ሻማዎቹን ለኮስናቸው።



*canoe* (ከኑ፡)
ታንኳ/በውሃ ላይ የሚንሣፈፍ
He paddled the canoe up the river.
ታንኳውን በወንዙ ላይ ቀዘፈ።



*cap* (ካፕ)
1. ጭንቅላት ላይ የሚደረግ ኮፍያ/መለዮ/ቆብ

He did not wear his cap.
ኮፍያውን አላደረገም፡






2. ክዳን/የብእር/ የጠርሙስ
I lost my pen cap. Have you seen it?
የእስክሪብቶ ክዳኔን ጣልኩት
አይተኸዋል?

*car* (ካ:ር)
መኪና
My uncle bought a new car.
አጎቴ አዲስ መኪና ገዛ።



*caravan* (ካረቫን)
በመኪና የሚጎተት ተንቀሳቃሽ ቤት
They are living in caravan.
በተንቀሣቃሽ ቤት ውስጥ ይኖራሉ።



*card* (ካ:ድ)
1. ጠንካራ ወረቀት/ካርድ/
This shoe box is made up of card.
ይህ የጫማ ሳጥን ከጠንካራ ወረቀት የተሰራ ነው።
2. የመታወቂያ ወረቀት
If you want to pass this gate please show me your card.
ይህን በር ለማለፍ ከፈለግህ እባክህ
መታወቂያህን አሣየኝ።
3. የስጦታ ካርድ/የገና/የልደት/ካርድ
I like to get cards on my birthday.
ለልደቴ ካርዶችን ማግኘት
እፈልጋለሁ።



4. የመጫወቻ ካርታ
I enjoy playing cards.
ካርታ መጫወት ያስደስተኛል።



*care* (ኬየ)
በጥንቃቄ መያዝ፤መንከባከብ/
አዛውንቶችን/በሽተኞችን/ልጆችን
My mother took care of me when I was ill.
የታመምኩ ጊዜ እናቴ ተንከባክባ
ኛለች።

*carol* (ካረል)
የገና መዝሙር
I love to sing carols at Christmas.
በገና የገና መዝሙር መዘመር ደስ ይለኛል።

*carpet* (ካ:ፒት)
ስጋጃ/ቤት ውስጥ ወለል ላይ የሚነጠፍ ምንጣፍ
My sister has a carpet on the floor of her house.
እህቴ ቤቷ ወለል ላይ ስጋጃ አንጥፋለች።




*carrot* (ካረት)
~~ካሮት~~/ ብርቱካናማ ቀለም ያለው መሬት ውስጥ የሚበቅል ስር
Lydia likes to eat carrots.
ሊዲያ ካሮት መብላት ትወዳለች።



*carry* (ካሪ)
በጀርባ ወይም በጭንቅላት መሸከም
I can't carry my bag. It is very heavy.
ቦርሳዬ በጣም ከባድ ስለሆነ ልሸከመው አልችልም።

*cart* (ካ:ት)
ጋሪ/በፈረስ ወይም በበሬ የሚጎተት ተሽከርካሪ
The donkey pulled the cart slowly.
አህያው ጋሪውን በዝግታ ጎተተው።



*carve* (ካ:ቭ)
1. ከእንጨት/ከድንጋይ ቅርጻቅርጽ መስራት
The man carved a mask from a piece of wood.
ሰውየው ከእንጨት የፊት ቅርፅ ሰራ።
2. የበሰለ ስጋን መቆራረጥ/ ለመብላት/
My father is carving the fish for dinner.
አባቴ ለእራት አሣውን እየቆራረጠ ነው።

*case* (ኬይስ)
1.ጉዳይ/ አንድን ሰው የሚመለከት

ሁኔታ
If that is the case, you have to study hard.
ጉዳዩ ያ ከሆነ በጣም ማጥናት አለብህ።
2. የአንድ ዕቃ መያዣ ወይም ማንጠልጠያ
That is a beautiful camera case.
ያ ቆንጆ የካሜራ መያዣ ነው።

*cat* (ካት)
1. ድመት
My cat has a dish of milk every morning.
ድመቴ በየቀኑ አንድ ሰሃን ወተት ትጠጣለች።



*catch* (ካች)
1. በእጅ መያዝ/መቅለብ
I'll throw the ball and you can catch it.
እኔ ኳሱን እወረውርልሃለሁ አንተ ቅለብ።



*caterpillar* (ካተፒለ)
አባ ጨጓሬ/ቢያድግ ቢራቢሮ የሚሆን ትል
The fat, ugly caterpillar turned into a beautiful butterfly.
ወፍራሙና አስቀያሚው አባ ጨጓሬ በኋላ ቆንጆ ቢራቢሮ ሆነ።



*cattle* (ካትል)
የቀንድ ከብቶች/ላም፣ በሬ የመሳሰሉት/
The cattle will have plenty of food.
ከብቶቹ በቂ ምግብ ይኖራቸዋል።



*cave* (ኬይቭ)
ዋሻ/ በመሬት ወይም በተራራ ውስጥ ያለ ቀዳዳ
The lioness lives in a cave.
አንበሳዋ በዋሻ ውስጥ ትኖራለች።



*cement* (ሲ'ሜንት)
ከውሃ ተቀላቅሎ ድንጋይና ድንጋይ

የሚያጣብቅ ዱቄት/ሲሚንቶ/

They built the wall with bricks and cement.

ግድግዳውን በሲሚንቶና በሸክላ ገነቡ።



*cent* (ሴንት)

ሳንቲም

100 cents make one birr.

መቶ ሣንቲሞች አንድ ብር ይሆናሉ።

*centre* (ሴንተ)

የአንድ ነገር መሃከል

The question mark is at the centre of the circle.

የጥያቄ ምልክቱ በክቡ መሀል ላይ ነው።



*century* ('ሴንቸሪ)

ምእተ አመት/የመቶ አመት ጊዜ/ ክፍለ ዘመን/

We are now living in the twentieth century.

አሁን በ20ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነን።

*certain* ('ሰ:ትን)

1. እርግጠኛ የሆነ/ጥርጥር የሌለው

I am certain that man stole my book.


ያ ሰው መጽሃፌን እንደሰረቀኝ እርግጠኛ ነኝ።

*chain* (ቼይን)

ሰንሰለት/ለማሠሪያነት ክብ ክብ ሆነው የተያያዙ ሽቦዎች ወይም ብረቶች

The policeman put a chain around the prisoner's hands.

ፖሊሱ የእስረኛውን እጆች በሰንሰለት አሰረ።




*chair* (ቼየ)

ወንበር /አራት እግር ያለው ባለመደገፊያ ለአንድ ሰው መቀመጫ የሚሆን

Please sit down on the chair.

እባክህ ወንበሩ ላይ ተቀመጥ።



*chalk* (ቾክ)

ጠመኔ/ቾክ/ ጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፊያ ነጭ ነገር

The teacher used the chalk to draw a map on the board.

መምህሩ ጥቁር ሰሌዳው ላይ በጠመኔ ካርታ ሳለ።



*change* (ቼይንጅ)
መለወጥ/መቀየር
The caterpillar changed into a butterfly.
አባ ጨጓሬው ወደ ቢራቢሮነት ተለወጠ።

*charcoal* ('ቻ:ከውል)
ከሰል
Charcoal is a burning wood.
ከሠል የተቃጠለ እንጨት ነው።

*chase* (ቼይስ)
ማባረር/ማሳደድ
The cat chased the mouse around the room.
ድመቷ አይጧን በክፍሉ ውሰጥ አሣደደቻት።


*cheap* (ቺ:ፕ)
ርካሽ
I bought a book for 8 birr. And I bought a pen for one birr. So the pen is cheap.
መጽሃፍ በስምንት ብር ገዛሁ። እስክሪብቶ ግን በአንድ ብር ገዛሁ። ስለዚህ እስክሪብቶው ርካሽ ነው።

*cheek* (ቺ:ክ)
ጉንጭ/ከአይን ስር ከአፍንጫ ግራና ቀኝ ያለው የፊት ክፍል
His cheeks turns to red when he is afraid.
ሲፈራ ጉንጮቹ ቀይ ይሆናሉ።




*cheer* (ቼየ)
በደስታ መጮህ/እልል ማለት
The crowd cheered when their team won.
የሚደግፉት ቡድን ሲያሸንፍ ቲፎዞው በደስታ ጮኹ።

*cheese* (ቺ:ዝ)
አይብ/ ከወተት የሚገኝ ከዳቦና ከቅቤ ጋር የሚበላ
Goats' cheese has a very nice taste.
ከፍየል ወተት የሚገኝ በጣም ጥሩ ጣእም አለው።



*cheetah* ('ቺ:ተ)
አቦ ሸማኔ/ነብር የመሠለ ኅርንጉርጉር ከእንስሣት ፈጣኑ እውሬ/
The cheetah is the fastest animal


in the world.
አቦ ሸማኔ ከአለም ፈጣኑ እንስሣ ነው።



***chest*** (ቼስት)
ደረት/ከአንገት በታች ከሆድ በላይ ያለው አካል
The boxer has a broad chest
ቦክሰኛው ሰፊ ደረት አለው።




2. ሳጥን/ሳንዱቅ/ሙዳይ
The old man puts his money in a chest.
ሽማግሌው ገንዘባቸውን በሣጥን ውስጥ ያስቀምጣሉ።



***chew*** (ቹ፡)
ማኘክ/ምግብን በአፍ ውስጥ ማላመጥ
Chicken leg is good to chew on.
የዶሮ እግር በቀላሉ ይታኘካል።

***chicken*** ('ቺኪን)
የዶሮ ጫጩት/ሴት ዶሮ
The chickens have laid a lot of eggs this week.
ዶሮዎቹ በዚህ ሳምንት ብዙ እንቁላሎችን ጥለዋል።



***child*** (ቻይልድ)
ህፃን ልጅ/ትንሽ ልጅ
This child is going to school.
ይህች ልጅ ወደ ትምህርት ቤት እየሄደች ነው።




***chilli*** ('ቺሊ)
ሚጥሚጣ/ በጣም የሚያቃጥል በርበሬ የሚመስል ቅመም
I don't like to eat chilli.
ሚጥሚጣ መብላት አልወድም።

***chimney*** ('ቺምኒ)
የቤት ጭስ ማውጫ
The smoke from the chimney made everyone cough.
ከጭስ ማውጫው የሚወጣው ጭስ ሰውን ሁሉ አሣለው።



*chimpanzee* (ቺምፓን'ዚ:)
ጭላዳ/ሰው የሚመስል ጭራ የሌለው ዝንጀሮ
Chimpanzees are easy to train.
ጭላዳ ዝንጀሮዎችን ለማሰልጠን በጣም ቀላል ነው።



*chin* (ቺን)
አገጭ/ከአፍ በታች ያለው የፊት ክፍል
My brother's chin is covered with hair.
የወንድሜ አገጭ በፀጉር ተሸፍኗል።



*chip* ('ቺፕ)
1. የጠርሙስ ወይም የብርጭቆ ስብርባሪ
My sister chipped the cup when she hit it with a knife.
እህቴ ስኒውን በቢላ ስትመታው ተሠባበረ።
2. በስሱ የተቆራረጠ ድንች ጥብስ
I like chips.
የድንች ጥብስ እወዳለሁ።

*chocolate* ('ቾክለት)
1. ቸኮሌት
My mother gave me a piece of chocolate.
እናቴ የቸኮሌት ቁራሽ ሰጠችኝ።



*choose* (ቹ:ዝ)
ከብዙ ወይም ከሁለት ነገሮች አንዱን መምረጥ
Which pencil will you choose? The red one or the blue one?
የትኛውን እርሳስ ትመርጣለህ ቀዩን ወይስ ሰማያዊውን?

*chop* (ቾፕ)
መቁረጥ/መቆራረጥ/መከትከፍ
The woman chopped the carrot.
ሴትየዋ ካሮቱን ከተፈችው።



*church* (ቸ:ች)
ቤተክርስቲያን
I go to church every Sunday.
ሁልጊዜ እሁድ እሁድ ወደ ቤተ

ክርስቲያን እሄዳለሁ።



*cinema* ('ሲነመ)
ሲኒማ ቤት/ተንቀሳቃሽ ፊልም የሚታይበት ቤት/
Dad is taking us to the cinema tonight.
አባባ ወደ ሲኒማ ቤት ዛሬ ማታ ይወስደናል።

*circle* ('ስ:ክል)
1. ክብ የሆነ ነገር
The shape of a ball is circle.
የኳስ ቅርጽ ክብ ነው።



2. ቀለበት ቅርጽ
A ring and a wheel are circles.
ቀለበትና ጎማ ክብ ናቸው።



*city* ('ሲቲ)
ከተማ
Addis Ababa is the capital city of Ethiopia.
አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነው።



*clap* (ክላፕ)
ማጨብጨብ እጆችን በማጋጨት ድምጽ መፍጠር
We clapped our hands when he was singing.
እሱ ሲዘፍን እኛ አጨበጨብንለት።

*class* (ክላ:ስ)
1. አንድ ላይ የሚማሩ ተማሪዎች
The director told the class to keep quiet.
ዳይሬክተሩ ተማሪዎቹ ፀጥታ እንዲያከብሩ ነገራቸው።
2. የመማርያ ክፍል
This is my class.
ይሄ የኔ ክፍል ነው።

*classroom* (ክላ:ስሩ:ም)
መማሪያ ክፍል
This is my classroom.
ይሄ የኔ መማሪያ ክፍል ነው።

*claw* (ክሎ:)
1. የእንስሳት ጥፍር
The cat held the mouse in its claws.
ድመቷ አይጧን በጥፍሮቿ ያዘቻት።
2. ባለ መዶሻ ምስማር መንቀያ

The carpenter has a claw.
አናጺው ባለ ምስማር መንቀያ መዶሻ አለው።

*clay* (ክሌይ)
ጡብ/እንስራ የሚሠራበት አፈር/ሸክላ አፈር
The man left the clay bricks in the sun to dry.
ሰውየው ጡቦቹን እንዲደርቁ ፀሀይ ላይ ተዋቸው።

*clean* (ክሊን)
መጥረግ/መወልወል/ማፅዳት ንፁህ ማድረግ
The water in the river was clean.
የወንዙ ውሃ ንፁህ ነበር።
Kumsa helped his brother to clean the windows.
ኩምሳ ወንድሙን መስኮቶቹን ለማፅዳት አገዘው።

*clever* (ክሌቨ)
ብልህ/ጎበዝ
Abi is very clever. He is always first in our class.
አቢ በጣም ጎበዝ ነው። ሁሌ ከክፍላችን አንደኛ ነው የሚወጣው።

*cliff* (ክሊፍ)
ከመሬት በጣም ከፍ ያለ የድንጋይ ኮረብታ
The boy fell down the cliff and broke his leg.
ልጁ ከኮረብታው ላይ ወድቆ እግሩ ተሰበረ።



*climb* (ክላይም)
ወደ ላይ መውጣት መንጠልጠል
The boy climbed the lader.
ልጁ መሠላሉን ወጣ።



*clock* (ክሎክ)
ትልቅ ሰአት/የግድግዳ/ የጠረጴዛ/
I have a clock beside my bed.
ከአልጋዬ አጠገብ የጠረጴዛ ሰአት አለ።



*close* (ክለውስ)
1. መዝጋት
Please close the door.
እባክህ በሩን ዝጋው።
2. በጣም የቀረበ
My uncle lives close to us.
አጎቴ የሚኖረው እኛ አጠገብ ነው።

*cloth* (ክሎስ)
ጨርቅ/ሸራ

My mother used a cloth to wipe the table.
እናቴ ጠረጴዛውን በጨርቅ ጠረገች።



*clothes*(ክለውዝስ)
አልባሳት
My sister has lots of pretty clothes.
እህቴ ብዙ ቆንጆ ቆንጆ ልብሶች አሏት።



*cloud*(ክላውድ)
ደመና
Look at the black cloud. It is going to rain.
የጠቆረውን ደመና ተመልከት ሊዘንብ ነው።

*clown*(ክላውን)
1. ኮሚክ/አስቂኝ/አሜዋች
The clown wore a big nosc.
አስቂኙ ሰውዬ ትልቅ አፍንጫ ሰክቷል።



2. ሞኝ/ቂል
The clown boy likes laughing.
ሞኙ ልጅ መሳቅ ይወዳል።

*coast*(ኮውስት)
የባህር ዳር/የባህር ጠረፍ
The coast of Kenya is beautiful.
የኬንያ የባህር ዳርቻ ቆንጆ ነው።

*coat*('ከውት)
ኮት/ካፖርት
It is very cold today. My father is wearing his coat.
ዛሬ በጣም ስለሚበርድ አባቴ ካፖርቱን ለብሷል።



*cobweb*(ኮብዌብ)
የሸረሪት ድር
There were lots of cobwebs in the corners of the room.
በክፍሉ ማእዘኖች ላይ ብዙ የሸረሪት ድር ነበረ።



***cock*** (ኮክ)
አውራ ዶሮ/ወንድ ዶሮ/
The cock crows every morning.
አውራ ዶሮው ዘወትር ጠዋት ጠዋት ይጮሃል።



***coffee*** (ኮፊ)
1. ቡና 2. የተፈላ ቡና
My brother has coffee every morning.
ወንድሜ ሁሌ ጠዋት ጠዋት ቡና ይጠጣል።

***cold*** (ከውልድ)
1; ብርድ 2. ጉንፋን
It is very cold today.
ዛሬ በጣም ይበርዳል።

***collar*** (ኮለ)
ኮሌታ/ አንገት አካባቢ ያለው የሸሚዝ ወይም የኮት ክፍል/
I have a blue shirt with a white collar.
ሰማያዊ ሆኖ ነጭ ኮሌታ ያለው ሸሚዝ አለኝ።



***colour*** (ከለ/ር)
ቀለም/ከለር
I like blue colour.
ሰማያዊ ቀለም እወዳለሁ።

***colt*** (ከውልት)
የፈረስ ግልገል
My father has taken the colt to the field.
አባቴ የፈረሷን ግልገል ወደ ሜዳ ወሰዶት።



***comb*** (ከውም)
1. ፀጉርን ማበጠር
My mother told my sister to go and comb her hair.
እናቴ ለእህቴ ፀጉሯን እንድታበጥር ነገረቻት።
2. የፀጉር ማበጠሪያ
Havc you seen my comb?
ማበጠሪያዬን አይተሃል?



*come* (ከም)

1. መጣ/መምጣት

Has the bus come yet?

አውቶቡሱ ገና አልመጣም?

2. ና

Come over here and look at this bird.


እዚህ ናና ይህችን ወፍ ተመልከት።

*compass* ('ከም'ፖስ)

1. ብሶል/አቅጣጫ ማሣያ መሳሪያ/

We used the compass to find our way.

አቅጣጫችንን ለማወቅ ብሶል ተጠቀምን።




2. የሂሳብ መሳሪያ/ማክበቢያ

I used my compass to draw a circle.

ክብ ስእል ለመስራት ማክበቢያዬን ተጠቀምኩ።



*concrete* ('ኮንክሪ፡ት)

የብረት/አሸዋና ሲሚንቶ ድብልቅ የህንፃ መስሪያ

The new bridge is made of concrete.

አዲሱ ድልድይ በኮንክሪት የተሰራ ነው።

*contain* (ከን'ቴይን)

በውስጡ ያዘ

This box contains biscuits.

ይህ ሣጥን በውስጡ ብስኩቶች ይዟል።

*cook* (ኩክ)

1. ምግብን ማብሰል/መጥበስ/መቀቀል

My mother is cooking fish for dinner.

እናቴ ለእራት አሣ እየጠበሰች ነው።

2. ምግብ የሚሠራ ሰው /ወጥ ቤት/

My father is a cook.

አባቴ የምግብ ስራ ባለሙያ ነው።



*cool* (ኩ፡ል)

ቀዝቃዛ

The water is too hot. Wait until it is cool.

ውሃው በጣም ሙቅ ነው እስኪቀዘቅዝ ጠብቂ።

*copy* (ኮፒ)

መኮረጅ/አንድን ነገር እንዳለ መገልበጥ/ መቅዳት/

She copied the letter into her book.
ደብዳቤውን ደብተሯ ላይ ገለበጠችው።

*corn* (ኮ:ን)
1. የእህል ዘር /ስንዴ/አጃ/
Wheat, barley, oats, all are corns.
ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ፣ ሁሉም የእህል ዘሮች ናቸው።
2. በቆሎ
The corn is ready to go to the mill.
በቆሎው ለመፈጨት ደርሷል።



*corner* (ኮ:ነ)
1. ሁለት ግድግዳዎች የሚገናኙበት ቦታ
You can't find a corner in a circular house.
በክብ ቤት ውስጥ የሁለት ግድግዳዎች መጋጠሚያ ማግኘት አትችልም።
2. መዓዘን/ሁለት መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ/መታጠፊያ/
He drove the car too fast around the corner and had an accident.
መኪናውን መታጠፊያው ጋ በጣም ስላበረረው አደጋ ደረሰበት።


*correct* (ከ'ሬክት)
1. አንድን የተሠራ ስራን ማረም ለአስተማሪ የቤት/ የክፍል ስራን/ ፈተናን ማረም
The teacher corrected the test.
አስተማሪው ፈተናውን አረመው።
2. ትክክል ወይም ልክ መሆን
All my answers were correct.
መልሶቼ በሙሉ ልክ ነበሩ።

*cost* ('ኮስት)
አንድን ነገር ለማግኘት የምንከፍለው ነገር ወይም ዋጋ
My shoes costs hundred birr.
የጫማዬ ዋጋ መቶ ብር ነው።

*cot* (ኮት)
1. የህፃን አልጋ
The baby was sleeping in its cot.
ህፃኑ አልጋው ላይ ተኝቶ ነበር።




*count* (ካውንት)
መቁጠር
The children can count very well.
ልጆቹ በደንብ መቁጠር ይችላሉ።




***country*** ('ከንትሪ)
አገር
Ethiopia is an old country.
ኢትዮጵያ ጥንታዊት አገር ናት።

***cover*** ('ካቨ)
አንድን ነገር መሸፈን
She covered the food with cloth.
ምግቡን በልብስ ሸፈነችው።


***cow*** (ካው)
ላም/ወተት የምትሰጥ የቤት እንስሣ
He gets up early in the morning to milk the cows.
ላሟን ለማለብ በጠዋት ይነሣል።



***crab*** (ክራብ)
ሸርጣን/አስር እግሮችና ጠንካራ ሽፋን ያለው የባህር እንስሣ/
Crab is used for food in Americans.
በአሜሪካ ሸርጣን ለምግብነት ያገለግላል።



***crane*** (ክሬይን)
1. ክሬን/ የከባድ እቃ ማንሻ መኪና
The crane lifted the heavy box onto the lorry.
ክሬኑ ከባዱን ሳጥን የጭነት መኪናው ላይ አንስቶ ጫነው።



2. ረጅም እግርና አንገት ያለው ወፍ
A crane likes to eat fishes .
ክሬን አሣዎችን መብላት ይወዳል።



***crawl*** (ክሮ:ል)
1. ዳዴ ማለት/ በጉልበት እና በእጅ መሄድ
The baby crawled across the floor.
ህፃኑ ወለሉ ላይ ዳዴ አለ።
2. በዝግታ ተጓዘ/ለመኪና/
The bus crawled up the steep hill.
አውቶብሱ ዳገቱን በዝግታ ተጓዘ።

3. በደረቱ ተሣበ/እንደትል ወይም እባብ
The snake crawled slowly.
እባቡ በዝግታ ተሳበ።

*crayon* (ክሬየን)
ከለር/ባለቀለም እርሳስ
I am going to draw a ship with my crayons.
በባለ ቀለም እርሳሶቼ መርከብ ልስል ነው።

*cream* (ክሪ:ም)
ስልባቦት/ወተት በእቃ ሲቀመጥ ከላይ የሚሰፈው ወፈር ያለ ነገር/
Butter is made from cream.
ቅቤ ከስልባቦት ይወጣል።

*cricket* (ክሪኪት)
1. ክሪኬት /የእንግሊዝ ጨዋታ/
2. ፌንጣ/ዋዝንቢት በከፍተኛ ድምፅ የሚፈጥሁ
Crickets make a noise by rubbing their wings together.
ፌንጣዎች ክንፎቻቸውን እርስ በርስ በማሸት ከፍተኛ ድምፅ ያወጣሉ።



*cripple* (ክሪፕል)
የአካል ጉዳተኛ/እግሩ ወይ እጁ የተጎዳ/
He was crippled by illness.
በህመም የአካል ጉዳተኛ ሆነ።

*crisp* (ክሪስፐ)
ደረቅ/እርጥብ ያልሆነ
These biscuits are very crisp.
እነዚህ ብስኩቶች በጣም ደረቅ ናቸው።

*crocodile* (ክሮከዳይል)
አዞ
A corocodile has a thick skin, short legs and a long tail.
አዞ ወፍራም ቆዳ፣ አጫጭር እግሮችና ረጅም ጭራ አለው።




*crooked* (ክሩኪድ)
1. የጎበጠ/የተጣመመ/የታጠፈ
We could not use the piece of wood. It is crooked.
ቁራጩ እንጨት ስለጎበጠ ልንጠቀምበት አልቻልንም።
2. አጭበርባሪ/የማይታመን/ህገወጥ
Don't believe Alemu he is a crooked man.
አለሙን አትመነው አጭበርባሪ ነው።

*cross* (ክሮስ)
መስቀል
You can see a cross on the edge of a church.
ቤተ ክርስቲያን አናት ላይ መስቀል

ማየት ትችላለሁ።



***crow*** (ክረው)
ቁራ/ጥቁር የወፍ ዘር/
The crow chased away the small birds.
ቁራው ትናንሾቹን ወፎች አባረራቸው።



***crowd*** (ክራውድ)
የሰው ክምችት
There was a large crowd at the football match.
በእግር ኳስ መጋጠሚያው ስፍራ ላይ ብዙ ሕዝብ ነበር።

***crown*** (ክራውን)
ዘውድ/የንጉስ ወይም የንግስት እራስ ላይ የሚጠለቅ
The king appeared wearing his gold crown.
ንጉሱ በወርቅ የተሠራ ዘውዱን አጥልቆ ቀረበ።



***cruel*** (ክሩ፡ወል)
1. ጨካኝ
The cruel man was kicking the dog.
ጨካኙ ሰውዬ ውሻውን ሲጠልዘው ነበር።
2. አሰቃቂ 3. የሚያም/የሚያሠቃይ

***crust*** (ክረስት)
1. ቅርፊት/የዳቦ/
I like the crust of a bread.
የዳቦ ቅርፊት እወዳለሁ።
2. በስሱ የተቀረጠ ዳቦ

***cry*** (ክራይ)
1. ማልቀስ/እንባን ማፍሰስ
She cries when she fell her exams.
ፈተናዎቿን ስትወድቅ ታለቅሳለች።
2. መጮኽ
'There is a snake in the garden,' cried the boy.
በአትክልቱ ቦታ ውስጥ እባብ አለ ብሎ ልጁ ጮኸ።

***cup*** (ከፕ)
1. ስኒ
My mother made us all a cup of coffee.
እናቴ ቡና በስኒ አዘጋጀችልን።



2. ዋንጫ/ በስፖርት ውድድሮች ለአሸናፊ የሚሰጥ

Ethiopia took the East and central African cup African in 2001.

ኢትዮጵያ በ1994 ዓ.ም የምስራቅና የመካከለኛው አፍሪካን ዋንጫ ወሰደች።

***cupboard*** ('ከበድ)

ቁምሳጥን

When my mother opened the cupboard it was full of tins, bottles and bags.

እናቴ ቁምሣጥኑን ስትከፍተው ጣሳዎች፣ ጠርሙሶችና ቦርሳዎች ነበሩት።



***curly*** (ኮ፡ሊ)

የተጠቀለለ ነገር በተለይ ፀጉር

Fofy has a curly hair.

ፎፊ የተጠቀለለ ፀጉር አለው።

***curve*** (ከ፡ቭ)

1. ኩርባ/ታጠፈ/ጎበጠ 2. ዞረ

The road up on the mountain has many curves in it.

በተራራው በኩል ያለው መንገድ ብዙ መታጠፊያዎች አሉት።



***cut*** (ከት)

መቁረጥ

She cut the picture out of the newspaper.

ስዕሉን ከጋዜጣው ላይ ቆርጣ አወጣችው።



# Dd

*D,d* (ዲ)
የእንግሊዝኛ አራተኛው ፊደል

*dad* (ዳድ)
አባቴ/ አባዬ/ አባባ
My dad works in an office.
አባቴ ቢሮ ውስጥ ይሰራል።

*dairy* ('ዴየሪ)
ወተት ወደ ቅቤና አይብ የሚለወጥበት ፋብሪካ/የወተት ፋብሪካ
At the dairy they make butter and cheese .
በወተት ፋብሪካው ቅቤና አይብ ይሠራሉ።

*dam* (ዳም)
ግድብ/ፈሣሽ ውሃ አንድ ቦታ እንዲጠራቀም የሚሰራ ግንብ
The dam burst and flooded the village.
ግድቡ ፈርሶ ሰፈሩን ውሃ አጥለቀለቀው።

*damage* ('ዳሚጅ)
አንድ የተሰበረ/የተበላሸ ጉዳት የደረሰበት ነገር
The car is badly damaged in the crash.
በአደጋው መኪናዋ በጣም ተጎዳች።

*damp* (ዳምፕ)
ረጠብ ያለ ጥቂት ውሃ ያለበት
She wiped the dishes with a damp cloth.
ሰሃኖቹን ረጠብ ባለ ጨርቅ ጠረገች።

*dance* (ዳ:ንስ)
መደነስ/ሙዚቃን ተከትሎ ሰውነትን መወዝወዝ/
I love to dance by quick music.
በፈጣን ሙዚቃ መደነስ እወዳለሁ።



*danger* ('ዴይንጀ)
አደገኛ/ሊጎዳን የሚችል ነገር
It is dangerous to play on the road.
መንገድ ላይ መጫወት አደገኛ ነው።

*dare* (ዴየ)
ደፈረ/ደፋር ሆነ
How dare you ride that wild horse.
እንዴት ብትደፍር ነው ያንን ያልተገራ ፈረስ የምትጋልበው?

*dark* (ዳ:ክ)
ጨለማ/ብርሃን የሌለበት/
It was very dark that night.
ያ ምሽት በጣም ጨለማ ነበር።

*date* (ዴይት)
አንድ ነገር የተደረገበት ቀን
What is the date of your birthday?
የተወለድክበት ቀን መቼ ነው?

***daughter*** ('ዶ፡ተ)
ሴት ልጅ
My aunt has three daughters.
አክስቴ ሶስት ሴቶች ልጆች አሏት።

***day*** (ዴይ)
1. 24 ሰአት/አንድ ሙሉ ቀን/ 12 ሰዓት ብርሃንና 12 ሰዓት ጭለማ
The baby is kept in the hospital for three days.
ህፃኗ ለሶስት ቀናት ሆስፒታል ቆየች።
2. ብርሃን ያለበት ጊዜ ከማለዳ እስኪመሽ ያለው
The sun shines all day.
ፀሃይ ቀኑን ሙሉ ታበራለች።

***dead*** (ዴድ)
የሞተ/ህይወት የሌለው የማይንቀሳቀስ ሰው ወይም እንስሳ/
The dead cat is laid at the side of the road.
የሞተችው ድመት ከመንገዱ ዳር ተጋድማለች።

***deaf*** (ዴፍ)
ጆሮው የማይሰማ/መስማት የተሳነው
The old man was deaf. He did not hear the car coming.
ሽማግሌው ጆሮአቸው መስማት ስለተሳነው መኪናው ሲመጣ አልሰሙትም።

***dear*** (ዲየ)
1. ደስ የምትል/የሚል/
I have a dear little puppy.
ትንሽ ደስ የምትል ቡችላ አለችኝ።
2. ውድ/ዋጋው በጣም ከፍተኛ የሆነ ነገር/
That radio is too dear. I cannot buy it.
ራዲዮው በጣም ውድ ነው። ልገዛው አልችልም።

***December*** (ዲ'ሴምበ)
ታህሳስ/በጎርጎርሣውያን የአመቱ 12ኛ ወር በኢትዮጵያውያን የአመቱ 4ኛ ወር/
We have school holidays in December.
በታህሳስ የትምህርት ቤት ዝግ አለን።

***decide*** (ዲ'ሳይድ)
አንድን ነገር ለማድረግ መወሰን
I cannot decide which dress to wear.
የትኛውን ቀሚስ እንደምለብስ መወሰን አልቻልኩም።

***decimal*** ('ዴሲ.ምል)
ከዜሮና ከአንድ መሃል ያለ ቁጥር ከነጥብ በኋላ የሚፃፍ
0.25 is a decimal number.
0.25 ከዜሮና ከአንድ መሃል ያለ ቁጥር ነው።

***deep*** (ዲ፡ፕ)
ጥልቅ/ወደ መሬት በጣም ርቀት ያለው ጉድጓድ
The miners worked deep underground digging out the coal.
የማዕድን ሰራተኞቹ ከሰል ለማውጣት ከመሬቱ ጠልቀው ይሠራሉ።

***deer*** (ዲየ)
አጋዘን/ረጃጅም ቀንዶች ያሉት የዱር እንስሳ/

The hyenas could not catch the deer.
ጅቦቹ አጋዘኑን መያዝ አልቻሉም።



*den* (ዴን)
ዋሻ/የዱር አራዊት መሬት ውስጥ ቆፍረው የሚኖሩበት ቤት/
The jackal hid in its den.
ቀበሮው በዋሻው ተደበቀ።

*dentist* ('ዴንቲስት)
የጥርስ ሀኪም
The dentist will take good care of your teeth.
የጥርስ ሃኪሙ ጥርስህን በደንብ ይንከባከብልሃል።



*describe* (ዲ'ስክራይብ)
አንድን ነገር በንግግር መግለፅ
Can you describe the man who stole your bag?
ቦርሣህን የሰረቀውን ሰው መግለጽ ትችላለህ?

*desert* ('ዴዘት)
በረሃ/በጣም ሞቃት የሆነና ምንም ነገር የማይበቅልበት ቦታ
Camels are the only animals which can cross the desert.
በረሃን ማቋረጥ የሚችሉ እንስሣት ግመሎች ብቻ ናቸው።

*desk* (ዴስክ)
ዴስክ/ተማሪዎች ተቀምጠው የሚማሩበት መፃፊያና መቀመጫ ያለው ወንበር/
The boy did his homework at his desk.
ልጁ ዴስኩ ላይ ሆኖ የቤት ስራውን ሰራ።




*destroy* (ዲ'ስትሮይ)
ማጥፋት/አንድን የነበረን ነገር እንዳልነበረ ማድረግ/
The fire destroyed the house .
እሳቱ ቤቱን አጠፋው።

*devil* ('ዴቭል)
ሰይጣን
Devil makes people to commit sin.
ሰይጣን ሰዎችን ሀጢአት እንዲሰሩ ያደርጋል።

*dew* (ድዩ:)
ጤዛ/ ዝናብ ሳይዘንብ ጠዋት ጠዋት ሳር ላይ የሚታይ ውሃ/
The dog left its footprints in the dew.
ውሻው በጤዛው ላይ የእግሩን ምልክት ተወ።

*diagonal* (ዲይ'አጎንል)
ተቃራኒ ማእዘናትን የሚያገናኝ ሰያፍ መስመር
The flag has two narrow diagonal lines.
ባንዲራው ሁለት ቀጫጭን አግድም መስመሮች አሉት።



*diameter* (ዳይ'አሚተ)
ክብ ነገርን ለሁለት እኩል የሚከፍል መስመር
The wheel was fifty centimetres in diameter.
የጎማው መሃል ርቀት ሃምሣ ሣንቲ ሜትር ነው።

*diamond* (ዳይመንድ)
አልማዝ/በጣም ውድ የሆነ የከበረ ድንጋይ/
She had three dimonds in her ring.
በቀለበቷ ላይ ሶስት የአልማዝ ቁራጮች አሏት።

*diary* ('ዳይየሪ)
የግል ገጠመኞችን መፃፊያ ደብተር/ ማስታወሻ መያዣ ደብተር
Mulu has kept a diary for the last five years.
ሙሉ ለአለፉት አምስት አመታት በማስታወሻ ደብተሯ ላይ ስትፅፍ ነበር።

*dice* (ዳይስ)
መጫወቻ ጠጠር/ ስድስት ቁጥር ከ1 እስከ 6 ነጠብጣብ ያላቸው ጎኖች ያሉት
The men were playing with dice.
ሰዎቹ በመጫወቻ ጠጠሮቹ ሲጫወቱ ነበረ።



*dictionary* ('ዲክሽንሪ)
መዝገበ ቃላት/ቃላት በቅደም ተከተል ከነትርጉማቸው ያሉበት መጽሃፍ
Good students always get a dictionary.
ጥሩ ተማሪዎች ሁልጊዜ መዝገበ ቃላት ይኖራቸዋል።

*die* (ዳይ)
መሞት/መተንፈስ ማቆም/
The man will die if you can not find him a doctor.
ሀኪም ካላገኘህለት ሰውየው ይሞታል።

*differ* (ዲፈ)
ከሌላ ነገር የተለየ
Square differes from a circle.
አራት መአዘን ከክብ ይለያል።

*difficult* (ዲፊከልት)
ለማድረግ/ለመስጠት አስቸጋሪ የሆነ ነገር
My brother finds it difficult to ride his bicycle.
ወንድሜ ብስክሌቱን መጋለብ በጣም አስቸጋሪ ይሆንበታል።

*dig* (ዲግ)
መሬትን መቆፈር
Before planting the tree you must dig a hole.
ዛፍ ከመትከልህ በፊት መሬቱን መቆፈር አለብህ።

*dim* (ዲም)
በጣም ብርሃን ያልሆነ በጣም ያልጨለመ/ ደብዘዝ ያለ
There is a dim light coming from the window.
በመስኮቱ ደብዘዝ ያለ ብርሃን ይገባል።

*dinner* (ዲነ:)
እራት/ሲመሽ የሚበላ ምግብ/
Come to my house for dinner tonight.
ዛሬ ማታ ለእራት እኔ ቤት እንድትመጣ።

*dinosaur* (ዳይነሶ:)
1. ከምድር የጠፋ ጥንታዊ ግዙፍ ፍጥረት
There are no dinosaurs alive today.
ዛሬ በህይወት የሚገኙ ዳይኖሰሮች የሉም።



*direction* (ዶሬክሽን)
አቅጣጫ/አንድ ነገር የሚገኝበት አካባቢ/
Which direction is north?
ሰሜን በየትኛው አቅጣጫ ነው?

*director* (ዳሬክታ)
መሪ ወይም ሃላፊ
The director of the school is a good man.
የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ጥሩ ሰው ነው።

*dirt* (ደ:ት)
ቆሻሻ/ንፁህ ያልሆነ
Clean that dirt from your dress.
ከቀሚስሽ ላይ ቆሻሻውን አፅጂ።

*disappear* (ዲሰፒየ)
መሰወር/በአይን ከመታየት መጥፋት/
The birds disappeared into the clouds.
ወፎቹ በዳመናው ውስጥ ተሰወሩ።

*discover* (ዲስከቨ)
አንድ ቀድሞ የማያውቁትን ነገር

ማወቅ/ማግኘት
Coffee is discovered by an Ethiopian.
ቡና መጀመሪያ የተገኘው በኢትዮጵያዊ ነው።

*dish* (ዲሽ)
ለሃን/ምግብ የሚቀርብበት ከብረት የሚሰራ/
Mami put the dish of stew on the table.
እማዬ ወጥ በሣህን ጠረጴዛው ላይ አደረገች።



*dishonest* (ዲስኦኒስት)
ከሀደት/ትክክል የሆነውን ትቶ ያልሆነውን ማድረግ/መናገር
It is dishonest to tell lies.
ውሸት መናገር ማታለል ነው።

*dislike* (ዲስላይክ)
መጥላት/አንድን ነገር አለመውደድ
I dislike eating porridge in the morning.
ጠዋት ጠዋት ገንፎ መብላት እጠላለሁ።

*distance* (ዲስተንስ)
ከአንድ ቦታ እስከ ሌላ ቦታ በመሃል ያለው ርቀት
What is the distance from Gambella to Mekele?
ከጋምቤላ እስከ መቀሌ ያለው ርቀት ስንት ነው?

*ditch* (ዲች)
ፉካ/ለውሃ መሄጃ የተቆፈረ መሬት/
Ditches prevent flooding.
ፉካዎች ከውሃ መጥለቅለቅ ይከላከላሉ።

*dive* (ዳይቭ)
ሰቶ መግባት/ ለዋና ተወርውሮ እጅን አስቀድሞ ውሃ ውስጥ መግባት/
My brother hurt his head when he dived into the pool.
ወንድሜ ተወርውሮ ውሃ ውስጥ ሲገባ ጭንቅላቱ ተጎዳ።

*divide* (ዲቫይድ)
1. አንድን ነገር ለሌላ ማካፈል
If you divide six by two you get three.
ስድስትን ለሁለት ስታካፍል ሶስትን ታገኛለህ።
2. አንድን ነገር መከፋፈል
Please divide the cake into four parts.
እባክህ ኬኩን ለአራት ቦታ አካፍለው።

*dizzy* (ዲዚ)
የአእምሮ መደንዘዝ/ ጭው ሲል
I felt dizzy as I looked down from the top of the tall tree.
ረጅሙ ዛፍ ላይ ሆኜ ወደታች ሳይ ጭው አለብኝ።

*do* (ዱ)
አንድን ነገር ማድረግ/መስራት
I will do my homework early tomorrow.
ነገ በጠዋት የቤት ስራዬን እሰራለሁ።

*doctor* (ዶክተ)
ሃኪም/ዶክተር የታመመን ሰው የማከም ትምህርት የተማረ
The doctor gave me medicine for my headache.
ሀኪሟ ለራስ ምታቴ መድሃኒት ሰጠችኝ።




*dog* (ዶግ)
ውሻ
The dog barked at the boy on the bicycle.
ውሻው ብስክሌት የሚጋልበው ልጅ ላይ ጮኸበት።




*doll* ('ዶል)
መጫወቻ አሻንጉሊት
My sister made a new dress for her doll.
እህቴ ለአሻንጉሊቷ አዲስ ልብስ ሰፋችላት።

*donkey* ('ዶንኪ)
አህያ/ለሸክም የምንጠቀምበት የቤት እንስሣ
Donkeys are small but they carry large loads.
አህዮች ትንንሾች ናቸው ግን ትልልቅ ሸክም ይሸከማሉ።



*door* (ዶ:)
በር/ወደ ቤት ወይም አንድ ቦታ መግቢያ/
He closed the door to keep the room warm.
ቤቱን ለማሞቅ በሩን ዘጋው።



*dose* (ዶውስ)
በአንድ ጊዜ የሚወሰድ የመድሃኒት መጠን
Ask the doctor about the dose of your medicine.

ለምትወስደው መድሃኒት መጠን ሃኪሙን ጠይቅ።

*dot* (ዶት)
ነጥብ/ነቁጥ
Remember to put a dot over your 'i's.
አይ(i) ላይ ነጥብ ማስቀመጥ አትርሳ!



*double* ('ደብል)
እጥፍ/ሁለት ጊዜ/
The price of butter is double than what was last year.
የቅቤ ዋጋ ባለፈው አመት ከነበረው እጥፍ ሆኗል።

*doubt* (ዳውት)
መጠራጠር/አንድ ነገርን መሆን ማድረግ መቻልን በማመንና በአለማመን መሃል መወላወል/
I doubt that I can jump the wall.
ያንን ግንብ መዝለሌን እጠራጠራለሁ።

*dove* (ደቭ)
እርግብ/ብዙ ጊዜ ጣራ ስር የምትኖር ወፍ/
The doves flew up into the tree.
እርግቦቹ ወደ ዛፉ በረሩ።



*down* (ዳውን)
ከከፍተኛ ቦታ ወደ ዝቅተኛ ቦታ መውረድ
He ran down the stair.
ከደረጃው ላይ በሩጫ ወረደ።



*doze* (ደውዝ)
እንቅልፍ መተኛት
My father likes to doze after dinner.
አባቴ ከእራት በኋላ መተኛት ይወዳል።

*dozen* ('ዳዘን)
ደርዘን/12 ነገሮች በአንድነት ሲሆኑ
I bought a dozen eggs in the shop.
አንድ ደርዘን እንቁላል ከሱቅ ገዛሁ።

*drag* (ድራግ)
መሬት ለመሬት ጎትቶ መውሰድ
He dragged the sack of potatoes to the barn.
የድንች ጆንያውን ጎትቶ ከከብቶች


ቤት አስገባው።

*drain* (ድሬይን)
ቦይ/ለውሃ መሄጃ የተቆፈረ
He poured the dirty water down the drain.
ቆሻሻውን ውሃ ቦዩ ውስጥ አፈሰሰው።

*drake* (ድሬይክ)
ወንድ ዳክዬ
My sister likes to feed the drakes.
እህቴ ወንድ ዳክዬዎቹን መመገብ ደስ ይላታል።



*draw* (ድሮ)
1. የአንድን ነገር ምስል መስራት
The boy is going to draw a picture of a bird.
ልጁ የወፍ ምስል ሊሠራ ነው።



2. በውድድር ሳይሸናነፉ መቅረት እኩል መውጣት
The two teams drew 2-2 on Wednesday.
ሁለቱ ቡድኖች ረቡዕ እለት ሳይሸናነፉ ሁለት ለሁለት ወጡ።

*drawer* (ድሮ:)
የቁም ሳጥን መሳቢያ
My father put My mother's clean shirts in the drawer.
አባቴ የናቴን ንፁህ ሸሚዞች መሳቢያ ውስጥ አስቀመጠ።

*dream* (ድሪ:ም)
ህልም/ተኝተው በእንቅልፍ የሚያዩት ነገር/
Some dreams are happy and some are sad.
አንዳንድ ህልሞች ደስ ይላሉ አንዳንዶቹ ያሳዝናሉ።

*dress* (ድሬስ)
1. ልብስ ማልበስ
Sara dressed her doll.
ሣራ አሻንጉሊቷን አለበሰቻት።
2. ቀሚስ/ ሴቶች የሚለብሱት ዘርፋፋ ልብስ/
My teacher was wearing a brown dress today.
ዛሬ አስተማሪዬ ቡና አይነት ቀሚስ ለብሳ ነበር።



*dribble* (ድሪብል)
1. ለሃጭ/ከአፍ የሚወጣ ዝልግልግ ፈሳሽ/
Babies always have dribble.
ህፃናት ሁልጊዜ ለሀጭ አላቸው።
2. ኳስን መሬት ለመሬት መግፋት ማንከባለል
The young players are learning

how to dribble the ball.
ወጣቶቹ ተጫዋቾች ኳስ እንዴት እንደሚያንከባልሉ እየተማሩ ነው።

*drill* (ድሪል)
ቀዳዳ መብሳት
My father drilled holes in the wood.
አባቴ እንጨቶቹ ላይ ቀዳዳዎች በሳ።

*drink* (ድሪንክ)
መጠጣት
Please don't drink all the water.
እባክህ ሁሉንም ውሃ አትጠጣ።

*drip* (ድሪፕ)
መንጠባጠብ/ለፈሳሽ ባንዴ ሳይሆን እየተቆራረጠ መውረድ/
The water dripped from the pipe.
ውሃው ከቧንቧው ውስጥ ተንጠባጠበ።



*drive* (ድራይቭ)
መኪና መንዳት ወይም በመኪና መውሰድ
I will drive you to the station in my uncle's car.
በአጎቴ መኪና እስከ መናኸሪያው እወስድሻለሁ።



*driver* (ድራይቨ)
ሹፌር/ መኪና የሚነዳ ሰው.
When I grow up I want to be a driver.
ሳድግ ሹፌር መሆን ነው የምፈልገው።



*drizzle* (ድሪዝል)
ካፊያ/ሃይለኛ ያልሆነ ዝናብ/
It drizzled all weekend.
ቅዳሜና እሁድን ሙሉ ሲያካፋ ነበር።

*drop* (ድሮፕ)
1. አንዷት ጠብታ
Only a few drops of rain came from the black cloud.
ከጥቁሩ ደመና ጥቂት ጠብታዎች ብቻ ዘነበ።
2. መጣል
The man dropped the brick on his foot.
ሰውየው ሸክላውን እግሩ ላይ ጣለው።

*drown* (ድራውን)
መስመጥ/በውሃ መታፈን/ ሰውነት በሙሉ በውሃ መሸፈን/
Many people drowned when the ship sank.
መርከቧ ስትሰምጥ ብዙ ሰዎችም በውሃ ታፈኑ።

*drum* (ድረም)
ከበሮ/ክብ እንጨት ላይ የተወጠረ መሀሉ ክፍት የሆነ ከቆዳ የሚሠራ የሙዚቃ መሣሪያ/

Misho plays the drum in the band.
ሚሾ በሙዚቃ ቡድኑ ውስጥ ከበሮ መቺ ነው።



*dry* (ድራይ/ድ)
ደረቅ/እርጥብ ያልሆነ/
Always light a fire with dry wood.
ሁልጊዜ በደረቅ እንጨት እሣት አያይዝ።

*duck* (ደክ)
ዳክዬ/በውሃ ላይ መንሳፈፍ የምትወድ ወፍ/
The duck took her babies into the water.
ዳክዬዋ ጫጩቶችዋን ወደ ውሃው ወሰደች።



*dumb* (ዳም)
መናገር የተሳነው የአካል ጉዳተኛ
There are special schools for dumb people.
መናገር ለተሳናቸው ሰዎች ልዩ ትምህርት ቤቶች አሉ።

*during* (ድይወሪን)
አንድ ነገር በሚደረግበት በዛው ጊዜ ሌላ ነገር ማድረግ
She fell asleep during the film.
ፊልሙ በሚታይበት ጊዜ እሷ ተኝታ ነበር።

*dust* (ደስት)
አቧራ/በአየር ውስጥ የሚበን/ ደቃቅ አፈር ወይም ብናኝ
My mother used a cloth to wipe the dust off the table.
እናቴ ከጠረጴዛው ላይ አቧራውን በጨርቅ ጠረገች።

*duster* (ደስተ)
ዳስተር/ የአቧራ መጥረጊያ ጨርቅ ወይም ብሩሽ
The boy cleaned the blackboard with a duster.
ልጁ ጥቁር ሠሌዳውን በዳስተር አፀዳ።



*dwarf* (ድዎ:ፍ)
ድንክ/ እድሜው ትልቅ ሆኖ ቁመቱ አጭር ሰው/
The dwarf sat in the child's chair.
አጭሩ ሰው የልጁ ወንበር ላይ ተቀመጠ።

*dye* (ዳይ)
ቀለም በመንከር የአንድን ነገር ቀለም መቀየር
We will dye these white shirts blue.
እነዚህን ነጫጭ ሸሚዞች ሰማያዊ ቀለም እንነክራቸዋለን።
አንድ ነገር ባለቤት/ ሃላፊ
The dog follcwed his master.
ውሻው ባለቤቱን ተከተለ።